# ጂኦግራፊ።
# Geografia

ለኢትዮጵያ ልጆች ጥቅም።
**for**
**the people of abyssinia**

ከኤሪክሶን።
**by**
**O. F. Erickson**

አስመራ
በሚሲኦንግ ስዌዴአ፥ ታተመ
፲፱፻፲፫።

**Asmara**
**SEWDISH MISSION**
**1921**

NIGUSS
DIGITAL LIBRARY

# ጂኦግራፊ።
# Geografia

ለኢትዮጵያ ልጆች ጥቅም።
for
the people of abyssinia

ከኤሪክሶን።
by
O. F. Erickson

አስመራ
በሚሲኦንግ ስዌዴአ፥ ታተመ
፲፱፻፲፫።
Asmara
SEWDISH MISSION
1921

# መቅድም።

አቤቱ፥ ስራህ እንደምን ብዙ ነው ሁሉን በጥበብ አደረግህ፥ ምድርም በባለጠግነት መላች። መዝ ፻፬፤ ፳፬።

በፍጥረት ሁሉ የእግዚአብሔር ጥበብና ክብሩ ቸርነቱም ይገለጥልናል፥ ይህነንም አስተውለን በንመለከት እግዚአብሔር ቅርባችን እንደሆነ እናያለን። እርሱ በትልቁም በትንሹም ነገር የሚፈልግ ሊናገረነ ነው። ደግ ልጅ አባቱ የሚናገረውን ይሰማል ስራውንም በደስታ ይመለከታል።

ይልቅ እኛ በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠርነ አእምሮ ለማስተዋል፥ ዓይን ለማየት ጆሮ ለመስማት፥ ከርሱ የተቀበልነ፥ ምነው የነን ከፍጥረቱ የምናገኘውን የሚያስደንቅ ነገር የማናይ

ከሁሉ በፊት ለገዛ አገራችን ኋላ ደሞ ለሌሎች ማወቅ ያስፈልገናል። ትንች ልጆች ካጥር ግቢያቸው በውጭ እንዴት ያለ ነገር እንዳለ በማየት ደስ ይላቸዋል። የኢትዮጵያ ሕዝብም ሌላ አገርና ሕዝብ ቢያውቁ፥ የገዛ አገራቸው ፍቅር አይጠፋቸውም። እውነተኛ ዓለማዊ እውቀት ደሞ እንዴት አድርገን ለገዛ ሕዝባችንና አገራችን እንደምናነቃ መንገድ ይከፍትልናል። እነዚያ እየብቻቸው የሆኑ ሕዝቦች እየተረዳዱ ወደ መሻልና ወደ ምላት እንዲደርሱ ደሞ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው።

ይህች መጽሕፈፍ በአቅምዋ ልክ የእግዚአብሔርን ክብር በፍጥረቱ ያላወቅነው አገርና ሕዝብ ደሞ ለማወቅ ልታግዘነ ትወዳለች። ጊዜ ስለ አጠረብነ ደሞ እንደ ትንሽ መግለጫ ናት እንጂ እንደሚገባ አልተሰናዳችም። ቈይታ ካስዋ የምትበልጥ ልትከተላት ተስፋችን ነው በሚቻለነ ነገር ሁሉ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ልንጠቅም ደሞ ፈቃዳችን ነው።

ከዚህ ስራ ያገዘኝ፥ ከትግርኛ ወደ አማርኛ የሚተረጐመው ደሞ መምህር ገብረ ክርስቶስ ተክለ ሃይማኖት ይህ ነው። ይህችን መጽሐፍ ለመጻፍ ለጣረና ለሚያነብዋ እያመገንሁ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ጥቅም ልትሆን ብዬ ተስፋ እያደረግሁ እደሰታለሁ።

አዲስ አበባ ጥቅምት ፲፱፻፲፫።

Of of Eriksson.

# ምድራችን።

ምድር በሞላው አንድ በጠፈር መካከል የሚዞር ክበብ ነው እንጅ አንዳንዶች እንደሚያስቡት ወለል ብሎ የተዘረጋ አይደለም። ይህነንም በባሕር ዳር ባለ ተራራ ወጥተው ቢመለከቱ ግልጥ ሁኖ ይታያል። በዚያ ሁነህ ያነን በፊትህ የነበረን መርከብ ብትመለከት ዘቅዝቆ የሚወርድ መስሎ ይታይሃል።

ያች የምታሞቅና የምታበራ ከምድራችንም፥ በጣም የምትልቅ ፀሓይ ለዓይናችን እንኳን የምትወጣና የምትገባ ቢመለን፥ ካንድ ሥፍራ ጸንታ የቆመች ናት። የምትዞር ምድራችን ናት በዚሁ ምክንያትም ቀንና ሌሊት በየፈንታው ይሆናል። ምድራችን በ፫፻፷፭ ቀን ወይም ባንድ ዓመት በፀሓይ ዙሪያ መዞርዋን ትፈጽማለች። ብርድና ሀሩር በየጊዜው የሚነሳ ደሞ፥ ምድራችን ወደ ፀሓይ በቀረበችና በራቀች ልክ ነው። ስለዚህ ደሞ በለዚያ በኤኳቶር (መካከለኛ የምድር ዙርያ) ያሉ አገሮች ሀሩር ይሰለጥናል። ከፖል አቅራቢያ ወይም በሰሜንና በደቡብ ጫፍ ባሉ አገሮች ግን ብርድ ይሰለጥናል ምክንያቱም ከፀሓይ መራቃቸው ነው። ለነዚያ የፀሓይ በጣም የማይመታቸው አገሮች የባሕር ጐርፎች ሙቀት ያደርስላቸዋል። ባሕር ለዓይናችን እንኳን የቆመ ቢመስል፥ ከመካከል በኤኳቶር ላይ የፀሓይ ኃይል በሚወድቅበት ውሀ ይሞቅና እንደ ብርቱ ጐርፍ ሁኖ ወደ ሰሜንና ወደ ደቡብ ይሄዳል። ፀሓይ ውሀ የምትስብ ስለ ሆነች የባሕር ውሀ አንዳንድ ግዜ ይጐላል አንዳንድ ግዜም ይሞላል። ከፀሓይ ሙቀት የተነሣ ውሀ ከባሕር ከቀላዮች ከወንዞችም ተስቦ ወደ ላይ ወደ አየር ወጥቶ እንደ ገና ወደ ምድር የሚወርድ። ያነን በፀሓይ ኃይል የተሳበ የውሀ ላበት ወደ ላይ ከወጣ በኋላ ከቀዝቃዛ አየር ይገናኝና ወፍሮ ወደ ደመና ይለወጣል፥ ደመና ከከበደ በኋላ ከሱ ውሀ ከምድር ያንጠበጥባል፥ ይህነንም ዝናም ይበላል።

ምድር በፀሓይ ዙርያ እንደምትዞር እንዲሁም ደሞ ጨረቃ ከፀሓይና ከምድር ዙርያ ትዞራለች። ጨረቃ እንዳንዳንዱ ከራሳቸው ብርሃን እንደ ሌላቸው ከዋክብት ብርሃንዋን ከፀሐይ ትቀበላለች። ስለዚህም አንዳንድ ግዜ ምድር ከፀሓይና ከጨረቃ መካከል ገብቶ ፀሓይ ብርሃንን ቢጋርዳት ጨረቃ ትጨልማለች።

## <u>የምድር መዓዝንቶች።</u>

የምድር ታላላቆች መዓዝንቶች ፬ ናቸው ፀሓይ የምትወጣበት ምሥራቅ፥ የምትገባበት ምዕራብ በዚህ መካከልም ሰሜንና ደቡብ አሉ። በምድር ስእል (ካርታ የኦግራፊ ያነን በስተ ላይ የሚገኝ ሰሜን ታችኛ ደቡብ፥ በስተ ቀኝ ምሥራቅ በግራ ምዕራብ እንደሆነ ማስተዋል ያስፈልጋል።

በቀን ፀሓይ በማትታይበት፥ በሌሊት ከዋክብት በማይታዩበት በባሕር ለሚሄዱ መምራት እጅግ የሚጠቅማቸው፥ ምድር መዓዝንቶችን የሚያመለክት ቡሶላ ወይ ኮምፓስ ነው። ከማመልከታቸው አንዱ ጫፍ በሰሜን ባለ ኤማንግ (ሳይታይ የሚስብ ኃይል) ተስቦ ወደዚያ ብቻ ያመለክታል። ሁለተኛ ጫፉ ደሞ በለዚያ በደቡብ ያለ ኤማግን ተስቦ ወደ ደቡብ ብቻ ያመለክታል።

በውሀ የተሸፈነ ስፍራ ከደረቅ ምድር ፫ ሩብ የሚያህል ነው። ስለዚህ ደረቁ ምድር ፩ ሩብ ነው።በዓለም በሞላው ያለ ህዝብ ቢቈጠር። ድምሩ ፩ ሺሕ ፰፻ ሚልዮን ያህላል።

## የዓለም ክፍሎች።

ዓለም ስማቸው እየብቻ በሆነ ፭ ክፍሎች የተከፈለች ናት። የነዚህ ክፍሎች ስም ደሞ እንዲህ ነው፤ አፍሪቃ አስያ ኤውሮጳ አሜሪካ፥ ኦቺኣኒኣ። እኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከአፍሪቃ ሕዝብ አንድ ክፍል ነነ። ኢትዮጵያ አንድ ክፍል ከምሥራቅ አፍሪቃ ደሞ ናት። አገራችን ኢትዮጵያ የተወለድንባት፥ ባባቶቻችን የቈየች ርስታችን፥ ከሌሎች አገር ይልቅ ክብርታችን፥ ለኛ የበለጠችና የምንወዳት አገራችን ናትና፥ አስቀድመን ይህችን አገር እንዴት እንደ ሆነች እንወቅ፥ እንመልከት እንመርምርም።

# ኢትዮጵያ።

ኢትዮጵያ ያለች ከምሥራቅ አፍሪቃ ናት። ደምበራቸው ከስዋ ጋር የሆነ አገሮች የሚከተሉት ናቸው በሰሜን ኤሪትሬኣ፥ በምሥራቅና ደቡብ የሱማል አገርና ኡጋንዳ በምዕራብ የሱዳን አገር። እያሌ ቈላ አሉባት፥ በተቀረ ግን ኢትዮጵያ ደጋና ወይናደጋ ናት። ተራሮችና ዘቅዛቆች ዱሆች ሜዳም እልፍ እልፍ፥ እያሉ የሚገኙበት ደጋ ነው። አንዳንድ ተራሮች እስከ ፭ ሺሕ ሜትር ከፍ ያሉ አሉ። በራሳቸውም ኖዋሪ የማይቀልጥ ውርጭ ይገኛል። ከኢትዮጵያ ተራሮች ሁሉ ከፍ ያለ ያ ከጐንደር በስተላይ ያለ ራስ ዳሻን የተባለ ተራራ ነው። ቍመቱ ከባሕር ላይ ፭ ሺሕና ፮፻ ሜትር ከፍ ያለ ነው።

## የኢትዮጵያ ሕዝብ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ በትውልዳቸው ከሴም ዘር ናቸው። የጥንት መኖሪያቸው ደሞ በዓረብ አገርና በአቅራቢያዋ ነው የነበረ። እያሌ መቶ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት ከዚያ ተነስተው ወደ ደቡብ አቅንተው ከኢትዮጵያ መጡ ለነዝያ በኢትዮጵያ ይኖሩ የነበሩ ሕዝብም ወርሰው በዚያ ተቀመጡ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከለዝያ የሚበዙ የአፍሪቃ ሕዝቦች ከፍ ያሉ አእምሮና መልካም ስርዓት ያላቸው ሕዝብ ናቸው። ቍመታቸው ከፍ ያለ ረጃጅም፥ በተሎ የማይቸነፉ ደፋሮች ናቸው። ስለዚህ ደሞ ሌሎች የአፍሪቃ ሕዝቦች በእንግዳ ሕዝብ ተገዝተው ሳሉ የኢትዮጵያ አገር ግን እስከ ዛሬ የራስዋ መንግሥት ሁና ራስዋን ችላ ትኖራለች። ሕዝብዋም በገዛ አገራቸው ልጆች ይዳኛሉና ይገዛሉ።

አሁን ኢትዮጵያን የሚገዙ ክብርትና ልዕልት ንግሥተ ነገሥት እቴጌ ዘውዲቱ ያጤ ምንሊክ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ልጅ ናቸው። አልጋ ወራሽም ልዑል ራስ ልዑል ተፈሪ ናቸው። ሁለታቸው ባዲስ አበባ፥ የኢትዮጵያ መናገሻ ከተማ ይኖራሉ። ግዛታቸውንም አዲስ አበባን መናገሻው ኢትዮጵያንም በሞላው እየለማ ሊሄድ፥ ንግድ እንዲሰለጥን፥ እውቀት ሊበዛ ታላላቆች አደራሾች ሊያሰሩ ማለፍያ የሆኑ የባቡር መንገድ ከድንጋይ የተሰበሩ ተበጅተዋል ሊያስበጁም ይወዳሉ።

ለዚሁ ሰፊ አገር ለመግዛት የሚያግዙም እያሌ አማካሮች ከልዑል አልጋ ወራሽ በታች አሉ። ከለዝያ በከተማ ሊያገልግሉ የተሰጣቸው መኳንንት በቀር ደሞ በየተቀበሉት ስራ ዋኖች ሁነው መንግሥት ለማጽናት የተሾሙ ታላላቆች መኳንንት አሉ በተቀርም በያገራቸውና በየግዛታቸው ክፍል ካገሩ ገዢ በታች ሁነው ለሕዝብ የሚገዙና የሚዳኙ ሹማምንት ይገኛሉ።

ሕዝቡ ባንዳንድ ተጽፎ ያልተቈጠረ ሁኖ፥ ቍጥሩ በእርግጥ አይታወቅም እንጅ፥ የኢትዮጵያ ዜጎች በግምት ፲ ሚልዮን ያህላሉ።

## የኢትዮጵያ ወንዞች።

በኢትዮጵያ አያሌ ትልልቅ ወንዞች አሉ። አንዳንዱ ግን በጋ ሲሆን ያቋርጣል። አስቀድመን በስተ ሰሜን ያሉና ወደ ምዕራብ የሚሰፉ ሁለት ወንዞች እናመለክታለን። እርሳቸውም መረብና ተከዜ ናቸው። ያ ፊተኛው በኢትዮጵያ መንግሥት መካከልና በኤሪትሬአ መካከል አድርጎ ኵናማን አልፎ ተከዜን ጋራ ያብርና በሌላ አትባራ በሚባል ስም ተጠርቶ፥ ከበርበር አቅራቢያ ከትልቁ ወንዞች ከኒል ይገባል። ተከዜም ከላይኛው ትግሬ ጀምሮ ካያሌ ወንዞች ተጠራቅሞ በትግሬና በጠለምት መካከል አድርጎ ወደ ወልቃይት ዘቅዝቆ ይሄዳል በዚያ አድርጎም ወደ ሰቲት ባሕር ይወርዳል። ከመረብ ጋር በአትባራ ተገናኝቶ ደሞ ከኒል ወንዝ ይደባለቃል። አባይ የተባለ ትልቅ የኢትዮጵያ ወንዝም ከደምብያ ጀምሮ በጣና ባሕር አድርጎ ጐጃምን በምዕራብ፥ ቤገምድርን በምሥራቅ ሸዋም ደሞ በምሥራቅ ደቡብን ትቶ ተጠምዞ ደሞ ለጐጃም ደቡብ ትቶ ወደ ምዕራብ ፈሶ ከኒል ይገባል። ብርቱ ውሀ ያላቸው ብዙ የጐጃም ወንዞችም ከአባይ ይገባሉ። እንዲሁም ደሞ እንጀማ ባሲሎ፥ ሙገር፥ ጉደርና ዴራ የተባሉ የሸዋ ወንዞች ካባይ ጋራ ይተባበራሉ፥ በሱዳን ዳርቻም ከነዚህ ከደቡብ የሚመጡ ዲደሳንና ደቡሳ የተባሉ ወንዞች ይገናኛል። ያ ወንዝ በሱዳን ከገባ በኋላ፥ ባሕር ኤል-አስራክ ተብሎ ይጠራልና በሴናርና ከሚል አልፎ ከካርቱም ወደ ኒል ይፈሳል። በክረምት ስንኳ አንዳንደ ግዜ በሴናርና በካርቱም መካከል መርከቦችን ለማስኬድ እስኪበቃ ድረስ ይበረታል። እንደዚሁም አሞ የሚባል የሚያቋርጥ፥ ትልቅ ወንዝ፥ ምንጩ ከሰሜን ጋላ የሆነ፥ ወደ ደቡብ ሂዶ ከሩዶልፍ ከትልቅ ሐይቅ ይፈሳል። ከጋላ የሚጀምር ቢላተ የሚባል አነስ ያለ ወንዝ ደሞ ከአበ የተባለ ይፈሳል። ከጋላ ደጋ የሚነሱና ወደ ደቡብ አድርገው የሚፈሱ አያሌ ወንዞች አሉ። የታላላቆች ስምም ዳዋ፥ የደሪአ መስኖ፥ ወልማል፥ ዌቢ ማኔ፥ ወብም ናቸው። በሱማል ዳርም ሁላቸደሞ ሰርዶ የቤት ሳር ዋሪያት ብዙ ሌላ ዓይነትም አለ።

ከቈላ የሚገኝ የሚበቅል ነገር እጅግ ብዙ ነው። ስለዚህ ጥቂት ብቻ ጠርተን እንተዋለን። ዛፎች፤ ዋርካ፥ ባምቦ፥ ሾላ እንኮይ፤ እሼ ሳገድ ዋንዛ ወይባ ጥቁር እንጨት፥ አባሎ በለስና ስሌን ብዙ ሌላ ዛፍም ናቸው። ፍሬ የሚሰጡ ዛፎች፤ ሙዝ፤ ሎሚ ናርጌ፥ ትርንጎ የሱከር አገዳ፥ ቡን ጥጥ፥ ኮክ ብዙ ሌላ ዓይነትም አለ።

## የብረት ዓይነት።

እንደ ብረት ብርና ወርቅ እንደዚህ ያሉም የበለጠ በጋላ አገር ይገኛሉ። አሳምረውና አብዝተው እንዳያወጡት መሳሪያ የሌላቸው ሁነው እንጅ፥ የዚያ አገር ሰዎችም እንደ ችሎታቸው አውጥተው ይነግዱበታል። ከኢትዮጵያ እሳት የሚፈልቅባቸው ተራሮች ስለ ነበሩ ደሞ ባያሌ ስፍራ ዲን ይገኛል። ብዙ ጥቅም የሚገኝበት ክቡር የሆነ ድንግያ ክሰል ደሞ በኢትዮጵያ አለ። የከበረና ለብዙ ነገር የሚጠቅም ፓታሳ የተባለ ጨው የሚመስልም በደሉል ያለ ልክ ይወጣል። ከብዙ ዘመናት ለኢትዮጵያ የሚሆን ጌሌ የተባለ ጨውም፥ ከትግሬ በስተ ምሥራቅ፥ ከአርሆ ነው እየፈላና ተቈፍሮ ተጭኖ ሲሄድ የሚኖር።

## ሐይቆች።

በኢትዮጵያ ትልልቅ ሐይቆች ይገኛሉ። ያነን ከሁላቸው የሚበልጥ ሐይቅ ከጐንደር አጠገብ በደቡብ ወገን፥ ከደብረ ታቦር ደሞ በስተ ምዕራብ የሚገኝ ጣና የተባለ ነው። ጣና አያሌ ቤተ ክርስቲያን ያሉባቸው ደሴቶች አሉበት። ጥልቁ ፫፪ ሜትር ነው፥ ርዝመቱ ደሞ ፷፪ ኪሎ ሜትር ነው። የቀሩት ሐይቆች ስም ይህነን የሚከተል ነው፤ ጮሜን ከወለጋ ከአዲስ አበባና የወለጋ ዳር የሚገኙ ደሞ ወንጥሽና ደንዲ ናቸው። እለዝያ ቅርብ ለቅርብ የሆኑ ደምበል ቂም ሆራ፥ አብዲሻቶ፥ ሆራ ሻላ፥ አባሲ፥ አቤ፥ ጫሞና፥ እስቴፋኒ የተባሉ የሚገኑ ከደቡብ ጋላ ናቸው።

እህልና የሚዛመደው ነገር፤ ማሽላ፥ ባሕር ማሽላ፤ ደጉሳ፥ ጤፍ አደንጐሬ፥ በርበሬ። የሳር ወገን፤ ጋጃ ገረደገቦ፥ ሰንበሌ፥ ስርስራ፤ ጀጀገ፥ የቆቅ እሳር።

## የእንስሳ ዓይነት።

በኢትዮጵያ ብዙ ዓይነት እንስሳ ይገኛል። ከደጋ የሚኖሩ የቤት እንስሳ፤ በሬ፥ ላም፥ በግ፥ ፈረስ፥ በቅሎ አህያ አንዳድ ፍየል ደሞ። የውጭ እንስሳ ግን ጥንቸልና አንዳንድ ምዳቋ ባይሆን ሌላ እጅግ አይገኝም። ስጋ የሚበሉ እንስሳ ደሞ፥ ውሻ፥ ጅብ፥ ቀበሮ ናቸው የሚበዙ። ዖፎችም እንደነ ደሮ ቆቅና እርኩም እንዲህ ያሉ ሌሎችም።

የወይና ደጋ እንስሳ። የወይናደጋ የቤት እንስሳ እንደ ደጋው ናቸው። ብቻ መልካቸውና ጉልበታቸው እየብቻ ይሆናል። የውጭ እንስሳ ደሞ ሰሳ ድኩላ፥ ምዳቋ ጥንቸል እንዲሁ የመሰሉም ናቸው። ስጋ የሚበሉም ጅብ ቀበሮ አንዳንድ አንበሳና ነብርም ናቸው። ዖፎች ደሞ ደሮ ቆቅ ድርጭት ዋያ ቍራና ብዙ ሌላ ዓይነት የወንዝ ዖፎችም አሉ ፡

የቈላ እንስሳ። ከኢትዮጵያ ቈላ የሚገኙ እንስሳ ለማየታቸው ደስ የሚያሰኙ ትልልቅ ወፍራሞች የጠዱም ናቸው። የቤት እንስሳ ከፈረስ በቀር እንደ ደጋው ናቸው ግመልም ደሞ ትጨምርባቸዋለ። የውጭ እንስሳ እነዚሁ ናቸው ዝሆን፥ ጅራተ ቀጭን የበዳ ፈረስ የበዳ አህያ አጋዘን፥ ድንኩላ ምዳቋ ሰሳ ብዙ ሌሎችም። ስጋ የሚበሉ እነ አንበሳ ጅብ ነብር፤ ተኩላ ቀበሮ፥ አፍን እንደነሱ ያሉ ሌሎችም። ከቈላ ዖፎች እነዚህ የሚከተሉትን ስማቸው እንጠራለን ሰጐን፥ ጃግራ ቆቅ ዋልያ ኩቱና ብዙ ሌላ ዓይነት አሞራ ልክ የሌላቸው የወንዝ ዖፎችም አሉ።

የውሀ እንስሳ። ኢትዮጵያ ምንም እንኳን ባሕር ባይኖራት በእነዚ ትልልቅ ሐይቆችና ወንዞች ብዙ ከውሀ የሚኖሩ እንስሳና ዓሣ ሞልተዋል። ከወንዞች የሚገኝ ትልቅ እንስሳ ጉማሬ ነው።

ከውሀና ከምድር መርኖር የሚችሉ ደሞ አዞ፥ ኤሊና፥ እንቍራሪት ናቸው። የውሀ ዖፎች፤ የውሀ ዶሮና፥ ይብራ ሌሎች እኒህን የመሰሉም ናቸው። ከለዚያ ትልልቅ ሐይቆች ደሞ ብዙ ዓይነት ትልቅና ትንሽ ዓሦች ይገኛሉ።

የሕዝብ ማስተዳደርያ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ትዳር የበለጠ እርሻና ከብት ማርባት ነው። እርሻ የበለጠ በደጋና በወይናደጋ ነው። ከብት ማርባት ደሞ ይልቁን በቈላ ነው የሚሰለጥን። ካሁን በፊት ያልተለመደ የነበረ ብዙ የእጅ ጥበብና ንግድ ደሞ አሁን በያገሩ ይለመዳል።

ተሸጦ ወደ ውጭ አገር የሚሄድ ብዙ የንግድ እቃ አለ ቡን የበለጠ ከጋላና ከዘጌ እህል ግን ብዙ ለመሸጥ የሚበቃ ሳለ ወደ ውጭ አገር መሸጥ ከልክል ነው። ማር፥ ሰም፥ ቅቤ ላስቲክ፥ ጥጥ፥ ዝሆን ጥርስ፥ ቈዳ፥ ዝባድና ብዙ ሌላም።

ከውጭ ወደ ኢትዮጵያ የሚገባ የንግድ እቃ የበለጠ የልብስ ዓይነት፥ የጦር መሳሪያ፥ አረቂ፥ የሐር ፈትል ሱካር፥ ሻሂ፥ ሰዓት ወረቀት ብርሌና ብርጭቆ ስሐንና ፍንጃል፥ ላምባ ጋዝ ስጋጃና ብዙ የኤውሮጳ ሸቀጥ።

## የኢትዮጵያ ሕዝብ ሃይማኖት።

ከሶስተኛው መቶ ዓመት ከክርስቶስ ልደት በኋላ፥ አክሱም የኢትዮጵያ ራስ ከተማ ሳለ፥ ጀምረው የሚበዙ የኢትዮጵያ ሕዝብ ክርስቲያን ናቸው። ሃይማኖታቸውም ተዋህዶ ተብለዋል። ተዋህዶ ማለት አንድ ሆነ ማለት ነው። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን፥ የግብጽ ቤተ ክርስቲያን የመስኮብና የግሪክ ቤተ ክርስቲያኖችም ስለ አምልኮ ወይ ሃይማኖት በብዙ ነገር ይቀራረባሉ ፡

የኢትዮጵያ ማሕበር ከምስር ማሕበር አንድነት አላት። አንደኛይቱ ለሁለተኛይቱ በታችዋ ናት። ስለዚህ ደሞ የኢትዮጵያን አቡን ከጥንት ከኢትዮጵያ ንጉሥ እየተጠሩ በእስክንድርያ ከሚኖሩ ኤጲስቆጶስ እየተመረጡና እየተባረኩ ናቸው የሚመጡ። አስቀድሞ በኢትዮጵያ ሁለት አቡኖች የነበሩ አንዱ ከትግሬ በዓዲ አቡን፥ አንዱ ደሞ ከሸዋ ባዲስ አበባ። እንያ በትግሬ የነበሩ አቡነ ጴጥሮስ ይባላሉ። አሁን ብቻቸውን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ዋና ጠቅላይ ሁነው ያሉ አቡነ ማቴዎስ ናቸው። በኢትዮጵያ ደሞ ክህነትና ዲቁና የሚሰጥ በእጃቸው ነው። በሃይማኖት የሚነካ ነገርም እሳቸው ናቸው የሚዳኙ።

የኢትዮጵያ ካህናት ፲ እልፍ ያህላሉ። እጅግ ስልጣንም አላቸው። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ከድያቆናት ጋራ የሌለበት አገር ጥቂት ነው። በእሁድ የሚደረግ ቅዳሴም የበለጠ በጥዋት ነው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥንት ከአይሁድ ጋራ አንድነት እንደ ነበራቸው ቀዳሚትን እንደ እሁድ በማክበራቸው እንረዳለን። የቤተክርቲያናቸው አከፋፈል ደሞ እንደ አይሁድ ቤተ መቅደስ ነው። አያሌ ሽሕ ፍላሽ የተባሉ ሕዝብ የአይሁድ ወገን ደሞ የበለጠ በጎንደር አጠገብ ይገኛሉ። የበለጠ ስራቸው ደሞ ከብት ማርባትና ሸማ ስራ ነው።

በሃብታቸውና በመጻሕታቸው ብዛት ስማቸው የተጠራ ብዙ ገዳሞችም በኢትዮያ አልፈው አልፈው ይገኛሉ።

አምስተኛ ወይም ስድስተኛ እጅ ከኢትዮጵያ ሕዝብ እስላም ናቸው። እርሳቸውም በሁሉ አገር እልፍ እልፍ ብለው ይገኛሉ፥ የበለጠ ግን በውሎ፥ በአሩሲ በጉራጌና በሱማሊ፥ በሞላው ናቸው። ከጋላ ሕዝብ የሚበዙ ክርስቲያኖች ተብለው ሳሉ የክርስትና ብርሃን በምሉ ስላልወጣላቸው ብዞች ብዚያ የወረሱት የአረሚነት ልማድ ይመላለሳሉ ፡

እስልምና ከኢትዮጵያ መካከል ጥሶ ገብቶ በሕዝብ ሁሉ እንዳይተላለፍ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምራ መከልከያ ሆነችበ።

## ስለ ቋንቋ።

የኢትዮጵያ ከጥንት ቋንቋ ግዕዝ ናት ግን በዚህ ዘመን ከንግግር ቀርታለች። ቢሆን ግን በቤተ ክርስቲያናት በስዋ ይቀደሳልና መጻሕፍት ይነበባል። እስዋንም ደሞ ካህናት እንጅ ሕዝብስ ያስተውላትም።

አሁን በኢትዮጵያ ሕዝብ የሚነጋገርባቸው፥ በግዕዝ ልጆችም የሆኑ ቋንቆች አማርኛ፣ ትግርኛና ትግሬ አሉ ከለዚህ በቀርም ብዙ ሕዝብ የሚነጋገላቸው አገውኛና ጋልኛ ናቸው። ሌላም እየበቻ የሆኑ ያልሰለጠኑ ቋንቆች አሉ።

## <u>የኢትዮጵያ ክፍሎች።</u>

የኢትዮጵያ አገር ክፍሎች ብዙ ናቸው ከክፍሎቹ ትልልቅ የሆኑ ደሞ በስተ ስሜን ካሉ ጀምረን እንጽፋለን ትግሬ፥ ዋና ከተማው አድዋ፥ ሕዝቡ ፯ ሺሕ ያህላል። ትልቅ ከተማ ገዳምም አክሱም ሕዝቡ ፰ ሺሕ ያህላል። ትልቅ ከተማ ደሞ መቀሌ አለ፥ ሕዝቡ ፳ ሺሕ ያህላል። የትግሬ ዳርቻ በሰሜን የመረብ ወንዝ በደቡብ የተከዜ ወንዝ፥ በምሥራቅ ደንከል በምዕራብ ባዜን ነው።

ጠለምትና ወገራ ከትግሬ ወደ ደቡብ የሚገኙ ታናናሾች ያንዳንድ ደጃዝማች ማሳደርያ የሚያህሉ አገሮች ናቸው።

ከዚያ ወደ ደቡብ ያለ ደምቢያ ነው ዋና ከተማው ያ ጥንታዊ የኢትዮጵያ ነገሥት ዋና ከተማ ፵፬ አድባራት ያለው ጐንደር ነው። ትልልቅ ከተሞች፤ ጨልጋና ደንቀዝ ናቸው።

ከጣና ሐይቅ በምሥራቅ ያለ ያገር ክፍል ቤገምድር ነው። ዋና ከተማው ደብረ ታቦር። ትልልቅ ከተሞች፤ ይፋግ ማህደረ ማርያም ናቸው።

ከዚያ በስተ ደቡብ ደሞ፥ ጐጃም የተባለ ሰፊ አገር፥ ዋና ከተማው ደምበጫ አለ። ጐጃም ከብዙ ግዜ ጀምሮ የክርስቲያን አገር እንደሆነ እለዚያ በሱ ያሉ ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች ይመሰክሩልናል። ትልልቅ ከተሞች ደብረ ወርቅና ሞጣ ናቸው።

ከጐጃም ወደ ምሥራቅ ደቡብ ያለ ደሞ ሽዋ ነው። ዋና ከተማው አዲስ አበባ። የአዲስ አበባ ሕዝብ ከ፹ ሺሕ የሚበልጥ ነው። ከአዲስ አበባ ከየደብሩ በቀር ስድስት ትምህርት ቤቶች አሉ። የአዲስ አበባ ቤተ ክርስቲያኖች ፲፯ ናቸው። በሽዋ ያሉ ትልልቅ ከተሞች አዲስ አለምና አንኮበር ናቸው።

ከሽዋ በስተ ምዕራብ የሚገኝ ያገር ክፍል ደሞ ወለጋ ጋላ ነው። ዋና ከተማው፤ ነቀምቴ። ትልልቅ ከተሞች፤ ድሬን ናደ፥ ቤኒና ሻንጉል ናቸው።

ከሽዋ በስተ ደቡብ ጉራጌ፥ ከዚያ ወደ ደቡብ ደሞ ወላሞ የተባሉ ትንሽ ያገር ክፍል አሉ። የጉራጌ ዋና ከተማ፤ ዘምበሮ ነው። የወላሞ ደሞ ዋቻሞ ይባላል።

ከወላሞ በስተ ደቡብ ደሞ ሲዳሞ የተባለ ትንሽ ያገር ክፍል አለ። ዋና ከተማው፤ አገረ-ሰላም።

ከሽዋ በስተ ምሥራቅ የደንከል አገር ይገኛል። ዋና ከተማው፤ ድሬዳዋ።

ከደንከል በስተ ምሥራቅ ደቡብ ያለ አገር ሱማል ነው ዋና ከተማው፤ ሀራር።

ከወላሞና ከጉራጌ በስተ ምሥራቅ የሚገኝ፥ አሩሲ የተባለ ሰፊ አገር አለ። ዋና ከተማው፤ አልባሶ።

ከትግሬ ወደ ደቡብም ዋግና ላስታ የተባለ በዋግሹም የሚገዙ አገሮች አሉ። ዋና ከተማ ሰቆጣ ነው፡

ከዋግ በስተ ደቡብ የጁ የተባለ ትንሽ ያገር ክፍል ይገኛል። ዋና ከተማው መርጦ ነው። ትልቅ ከተማ ደሞ ወልደያ የተባለ በዚያ አለ።

ከሽዋ በስተ ሰሜን ከየጁ በደቡብ ደሞ ወሎ የተባለ ሰፊ አገር አለ። ዋና ከተማው፥ ደሴ ነው። ትልልቅ ከተማ ቦሩና ወርኤሉ ናቸው።

ከትግሬ ወደ ደቡብ ምሥራቅ ዓዘቦና ዘቡል ናቸው። ያሁኑ ዋና ከተማ ማይጨው ነው። ትልልቅ ከተማ ጨርጨርና ቆቦ ናቸው።

### ኮሎኒያ ኤሪትሬአ።

ኮሎኒያ ኤሪትሬአ የኢታልያ ግዛት ናት። መጨረሻዋም፥ በምሥራቅ ቀይ ባሕር (ማር ሮሶ)። የጥንት ስሙዋ ግና ባሕረ ኤሪትሪአ ነው። በዚህ ምክንያት ደሞ ይህ ኮሎኒያ በዚህ ስም ተጠራ። በስተ ሰሜንም የእንግሊዝ ሱዳን የሚባል ደሞም በምዕራብ ከሱዳን ጋራ በስተ ደቡብም ከኢትዮጵያና ጅቡቲ የፈረንሳ ኮሎኒያ።

ይህች ኮሎኒያ ኤሪትሬአ ወደ ሶስት መቶ ሽህ የሚቀርቡ ባላገሮች አሉባት። ከነዚህው ግና ከእኩል የሚበልጡ እስላሞች ናቸው። መቶ ሽህ የሚያህሉ ኦርቶዶክሳውያን ናቸው። ሀያ ሽህ የሚሆኑ ካቶሊካውያን። ሁለት ሽህ ስድስት መቶ የወንጌል ክርስቲያን። ዐስራ አምስት ሽህ ግና አረማውያን ናቸው።

እነዝያ በባሕር አጠገብ ያሉት ቋንቋቸው አረብኛ ነው። በሰሜን እኩል ያሉትም ትግሬ። በምዕራብ ብሌን፥ ብንዓምር፥ ኩናማ። እንያ የደቡብም ቋንቋቸው ትግሪኛ ነው የኮሎንያ ራስ ከተማም አስመራ በዚያ ያሉ ሕዝብ ፲፭ ሽሕ የሚያህሉ ናቸው።

ኤሪትሬአ በየኮሚሳሪዮች ግዛት የተከፈለች ናት እርሳቸውም የሚከተሉቱ ናቸው።

በምሥራቅ ወገን ሰምሃርና ሌሎች ባቅራብያው ያሉ አገሮች ዋና ከተማዪቱ ምጥዋ፥ እርስዋም ትልቅ የኤሪትሬአ ወደብ ናት።

በደቡብ ምሥራቅ ወገን ደንከል፥ ዋና ከተማዪቱ ዓሰም።

ከደንከል ወደ ሰሜን ምዕራብ ያለ የአሳውርታና የእኰለጕዛይ አገር ዋና ከተማዪቱ ዓዲ ቀይሕ ነው።

ከእኰለጕዛይ በሰሜን ያለ አገር ክፍልም ሐማሴን ነው ዋና ከተማዪቱ አስመራ።

ከሐማሴን በስተ ደቡብ ያለ አገር ሰራዬ፥ ዋና ከተማዪቱ ዓዲ ኡግሪ ናት።

ከሐማሴን በስተ ሰሜን ያሉ አገሮች መንሳዕ፥ በጎስ ባቅራቢያቸው ያሉ አገሮችም ዋና ከተማዪቱ ከረን ናት።

ከበጎስ በስተ ስሜን ያለ ትንሽ አገር ክፍልም ሐባብ ነው ዋና ከተማዪቱም ናቅፋ ናት።

ከበጎስ በስተ ምዕራብ ያለ አገርም አልገዴን ይባላል ዋና ከተማዪቱም አቅርደት ናት።

ከአልገዴን በምዕራብ ደቡብ ያለ አገርም ባዜን ነው። ዋና ከተማዪቱም ባሬንቱ ናት።

ኮሎንያ ኤሪትሬአ እለዚያ በስዋ ያሉ የኢታልያን መንግሥት የካቶሊካውያን ማሕበርና የሱዌድ ወንጌላዊት ማሕበር ትምህርት ቤቶች ስላሉ በብልህነት መንገድ ልትራመድ ጀምራለች።

## አፍሪቃ።

አገራችን ኢትዮጵያ ያለችበት ትልቅ የዓለም ክፍል፥ አፍሪቃ ይባላል። አፍሪቃ ከለዚያ ብዙ አገሮችና ሕዝቦች ሰብስበው ይዘው እንዳሉ የዓለም ክፍሎች ትልቅ የዓለም ክፍል ነው እንጅ፥ እንደ ማንም አገር አይዶለም።

የአፍሪቃ ዳርቻ በሰሜን መካከለኛ ባሕር በምሥራቅ የኤትራ ባሕርና የህንድ ውቅያኖስ በምዕራብ የአትላንቲክ ውቅያኖስ በደቡብ ደሞ የአትላንቲክና የህንድ ውቅያኖስ አሉ።

ከሰሜን አንስቶ እስተ ደቡብ የአፍሪቃ ርዝመት ፰ ሺሕ ኪሎ ሜትር ነው። ወርዱም ከምዕራብ ዳርቻ እስተ ምሥራቅ ፯ ሺሕና ፭፻ ኪሎ ሜትር ነው። የሁሉ መሬቱን ስፋት ፴ ሚልዮን ሜትር ኳድራት ነው። የዙርያው ገመገም ርዝመት ፲፮ ሺሕ ፩፻፹፩ ኪሎ ሜትር ነው።

ባሕር ከውስጥ አገር የማይገባበት ስለ ሆነ፥ በገመገሙ ጥቂቶች ወደቦች (ፋርዳ) ብቻ ይገኙበታል። ወንዞቹ መራክቦች ለማሳለፍ የማይበቁ ስለ ሆኑ፥ በመርከብ ወዳገር መግባት የሚያስቸግር ነው። የብረት መንገድ እንደ ሌሎች ዓለም ክፍል ያለ ገና በብዙ ስፍራ አልተበጀም ግን እየተሰራ ይሄዳል። በዚያ ልክም ባገሮች ብልህነት ይገባል።

ከአፍሪቃ ብረት መንገድ ሁሉ የሚረዝም ላገር ሁሉ የሚያለማ አእላፋት ሕዝብን የሚጠቅም፥ ያነን ከካጽ የምትባል ከተማ ከደቡብ አፍሪቃ ጀምሮ በአፍሪቃ መካከል አልፎ እስከ ካይሮ የምትባል የምስር መናገሻ ከተማ የሚደርስ የብረት መንገድ ነው።

በሚከተሉ ክፍሎች ስለ አፍሪቃ ባህርያት ሕዝቡና አገሮቹ እንናገራለን።

## የአፍሪቃ ባህርይ።

አፍሪቃ እንደ ከፍታውና እንደ ዝቅታው መጠን፥ በየስፍራው እንደ አቀማመጡ፥ አየሩ የተለያየ ነው።

አፍሪቃ ብዙ ዓይነት የሆኑ፥ እርሱ ከርሳቸው የተራራቁ፥ የማይመሳሰሉ ሕዝቦችን የያዘ አገር ነው። የሕዝቡ ባህርይ እንዴት መሆኑን ብንመለከት እንደ መልኩ ልዩነት ሁኖ እናገኘዋለን። በአፍሪቃ ፍርያም መሬትና ሰፊ ያሸዋ በረሃ ይገኛል። ከፍሪቃ ቈላና ደጋ ቅርብ ለቅርብ ሁነው ይገኛሉ ከሌሎች የዓለም ክፍል ግን እንዲሁ አይዶለም። በስተ ደቡብ ካሉ አገሮች ጀምረን እናመለከታለን።

## አፍሪቃ ደቡብ።

እርሱ ከፍ ያለ ሜዳ የሚመስል ስፋቱ ደሞ የአፍሪቃ ሩብ ነው። ለደጋው ከባሕርና ከመካከለኛ አፍሪቃ የሚለዩት እነዚያ ከፍ ያሉ የተራሮች ተሬ ናቸው። አያሌ ወንዞችም ካገር ተነስተው በተራሮቹ አልፈው ከባሕር ይፈሳሉ።

ያ አገር እንደ መሰላል ከፍ ከፍ እያለ የሚሄድ ነው። ያ ከባሕሩ ዳር ያለ አገር ቈላ ነው። ካገር ውስጥ ስትገባ፥ ባጽዋርትፈልድ የሚባሉ ተራሮች ይታለፍና፥ ወደዚያ ካሮ የተባለ ሰተት ያለ ፩ ሺሕ ፭፻ ሜትሪ ከባሕር ከፍ ያለ ሜዳ ይደርሳል። ኹፈልድ የተባለ የተራሮች ተሬ አልፎ ደሞ፥ ከዚያ ፰ ሺሕ ሜትሪ ከባሕር ከፍ ያለ ውስጥ አገር ይደርሳል። በምዕራቡ ወገን በዚያ አገር ካሊሃሪ የተባለ ሰፊ በረሃ አለ። በካሊሃሪ ዳርቻ የድራኼን ተራሮች የተባሉ ተቀጣጥለው ከምሥራቅ ወደ ሰሜን አድርገው የተዘረጉ ተያይዘዋል።

## መካከለኛ አፍሪቃ።

መሀከለኛ አፍሪቃ የሚባል ካሳምቤሲ ወንዝ ጀምሮ እስተ ሰሃራ በረሃ የሚደርስ ነው። ወደ ሰሜን አድርጎ እየተተከለ ይሄድና ወደ ሰፊ ቈላ ይለወጣል። መሀከለኛ አፍሪቃ እንደ መሬቱ ዓይነት ካ፬ ይከፈላል፤ የምሥራቅ አፍሪቃ ደጋ፥ ከኮንጎ ወንዝ ያለ ወለል ያለ ሜዳ የጕኔኣ ደጋ ደሞ እስከ ጕኔኣ ጕልፍ፥ በሰሜንና በምሥራቅ ወገን የሱዳን ቈላ ነው።

የምሥራቅ አፍሪቃ ደጋው የሚበዛ ሜዳ ነው። ያ ሜዳም ዝቅ ባሉ የተራራ ተሬ ይከፈላል። ከመካከለኛ የምድር ዙርያ (ኤኳቶር) ግን በተርታ ሁነው የተከታተሉ ትልልቅ የሞላው አገር ይለውጣል። ያ ከፍታው ፯ ሺሕ ሜትር የሆነ ኪሊማንጃሮ የተባለው ተራራ ደሞ መሰረቱ ከዝያ ነው። የትልቁ የምስር ወንዝ ምንጭ ደሞ ከዝያ የሚጀምር ይመስላል። ይህ ደጋ እየቀጠለ ከኢትዮጵያ ደጋ ይገጥማል። እርሱ ደሞ እልፍ እልፍ ብሎ ከባሕር ፫ ሺሕ ሜትር ከፍ የሚል ስፍራ አለበት። ያንዳንዱ በዚያ ያሉ ተራሮችም ውርጭ የተሸፈነ ነው። ያነን በኮንጎ ያለ ሜዳ በክረምት ውሀ ሞልቶ ቀምበይበይ ይላል። የጕኔኣ ደጋ ከለዚያ ከምዕራብ አፍሪቃ ወደ ደቡብ አድርገው የሚዘነብሉ ተራሮች ይተባበራል። ያነን ባጠገቡ ያለ የካሜሩን አገር ደሞ እሳት የሚፈልቁ ተራሮች ይገኙበታል። ያነን ከላይኛው የጕኔኣ ደጋ መሀከልና ከኮንጎ ተራሮች መሀከል፥ ከኢትዮጵያ ደጋም መሀከል ያለ የሱዳን አገር ይባላል።

## <u>አፍሪቃ ሰሜን።</u>

አፍሪቃ ሰሜን ከሶስት ይከፈላል ሰሃራ የሚሉት ሰፊ በረሃ፥ ዴልታ የምሥራቅ ኒል፥ ከመሀከለኛ ባሕር ገመገም ያሉ አገሮች። ሰሃራ ፬ ግዜ ኢትዮጵያን የሚገመገም ያሉ አገሮች። ሰሃራ ፬ ግዜ ኢትዮጵያን የሚያህል ሰፊ የበረሃ አሸዋ ነው። ያነን በስተ ምሥራቅ ያለ በረሃ ሊብያ ይባላል። በበረሃው አልፎ አልፎ ከባሕር ዝቅ ያለና ሃሩር የሚበረታበት ምድር አለ። ግን በዚያ ደሞ ደጋና ተራሮች ይገኛሉ። አንዳንድ ግዜም ይዘንማል። አልፎ አልፎም ውሀ ያለበትና ተምር የሚያፈራ ስሌን ያለበት ለምለም የሆነ ኦዓሲ የተባለ ስፍራ ይገኛል። ግን ሲሄዱ ሰንብቶ ከአሸዋና ደንግያ በቀር ነጥብ ውሀ ሆነ የሚበቅል ነገር የማይታይበት ሰፊ ስፍራ ደሞ ይገኛል። ከምስር ዴልታ አጠገብ ተምር የሚያድረአ ስሌን የመሉባቸው ኦዓሲ አሉ። የሊብያ ተራሮች አንዳንድ ዳርቻ ሁነው በረሃውን ከምስር ዴልታ ይለየዋል።

የአፍሪቃ ሰሜን ገመገም የሚበልጥ በተርታ የሆኑ ተራሮች የሞሉት ነው። ከምስር በስተ ምዕራብ እስከ ባሕር የሚደርስ ሜዳ አለ፥ እርሱ ደሞ ከፍ እያለ ይሄድና ከባርካ ደጋ ይቀጠላል። ባርካ ከጥንት መሬቱ ፍርያም በመሆኑ የተመሰገነ ችሬኔ ነው። ያነን የበረሃ አሸዋ እስከ የሲድራ ጎልፎ፥ ባሕሩን በትሪፖሊ ገባ በሚልበት ይደርሳል። የአትላስ ተራራ ከቱኒስ ጀምሮ ማሮኮ በሞላውን ያልፋል። በምዕራብ ወገንም እስከ ፫ ሺሕና ፫፻ ሜትር የሚያህል ከፍ እያለ ይሄዳል ከማሮኮ በስተ ሰሜንም በኖዋሪ ውርጭ የተሸፈኑ ተራሮች አሉ። ከመሀከለኛ ባሕር አጠገብ እጅግ ከፍ ያላለ ሪፍ የተባለ የተራሮች፥ ተሬ አለ። ከዚያ ወድያ ያ አገር አንደ ግዜ ሜዳ አንዳንደ ግዜም ተሬ እየሆነ ወደ ሰሃራ አርጎ ይገመገማል። የመሰሉ የወንዝ ዙርያ አልፎ አልፎ ውሀ የማይለቀው ቅዝቅ የሚመስል ነው። የኮንጎ ወንዝ ርዝመት ፭ ሺሕና <u>፫፻፶፮</u> ኪሎ ሜትር የኒገር ፬ ሺሕና <u>፮፻፳፱</u> ኪሎ ሜትር፥ የኒል ፬ ሺሕና <u>፱፻፫፫</u> ኪሎ ሜትር የሚበልጥ ነው። እነዚያ ታንጋንጂካ ሙኤሮና ባንግዌኦሎ የተባሉ ትልልቅ ወንዞች ደሞ ትርፍ ውሀቸው በኮንጎ ወደ ባሕር ይሰዳሉ። ስምበሲ ከምዕራብ ተነስቶ ወደ ባሕር ይሰዳሉ። ሳምበሲ ከምዕራብ ተነስቶ ወደ ምሥራቅ ይወጣና ባገሩ መሀከል ከትልቅ ገደል ተወርውሮ ይፈሳል፥ ይህነንም ለማየቱ የሚያስደንቅ ጉድ የሆነ ፍዋፍዋቴ የቢክቶሪያ ፍዋፍዋቴ ተብሎ ይጠራል። ያነን ኛሳ የተባለ ትልቅ ሐይቅ ባሺሬ የተባለ ወንዝ ውሀውን ወደ ሳምቤሲ ይሰዳል።

የኒል ወንዝ ከጥንት ጀምሮ ከሌሎች ወንዝ የበለጠ ግሩም የሆነ ወንዝ ነው። ኒል ዝናም በማይዘንብበት አገር ነው የሚጐርፍ፥ ግን ገምገሙን አልፎ የምስር አገር በሞላው የጠጣና አገሪቱን ሁልዋ ፍሬያም መሬት ያደርጋታል። የምንጩን ኃይል እለዚያ በአፍሪቃ ውስጥ ያሉ ትልልቅ ሐይቅ ናቸው። እንደነ ቢክቶሪያ ኒአንሳና አልበርት ኒአንሳ። የኒል ወንዝ እያንኳለለ ወደ ሰሜን አድርጎ ያልፋል ከሱዳን ያያሌ ወንዝ ውሀ ይቀበላል፥ ከካርቱምም ከዚያ በጣና አድርጎ ከኢትዮጵያ የሚወጣ አባይ የተባለ ወንዝ ይገናኛል። እልፍ ብሎም ከተከዜ ጋራ ወይም ከኣትባራ ይተባበራል። ከዚያ በኋላ ግን ከሌላ ወንዝ ሳይገናኝ እስከ መጨረሻው ፪ ሺሕ ኪሎ ሜትሪ የሚያህል መንገዱን ይቀጥላል።

የኒል ወንዝ ስላለ ዝናም የማይዘንምበት የምስር መሬት ብዙ ዓይነት ፍሬ የሚያፈራ ፍሬያማ መሬት ይሆናል። በሐምሌ ያ የወንዙ ውሀ ሊነሳ ይጀምራል፥ ከፍ እያለ ሂዶም በመስከረም አገሩን በሞላው ሐይቅ ያደርገዋል። ውሀው ከሚቻለው ስፍራ ሊገባ ብለውም ትልቅ ከደንግያ የተሰራ ብርቱ ድልድይ አደረጉበት። በተቀረው በእርሾች መሀከል ትልልቅ መስኖ ምሰውበታል። ለነዚያ ከፍ ያሉ እርሾችም በብልሓት በመዘወር አድርገው ውሀውን ያውጡላቸዋል። ያገሩ ፍሬ መሰብሰብ በያነን ውሀ ብርታት ልክ ነው። ጥለቱም በውሀው መጠን ነው የሚወድቅ። ከካይሮ አጠገብ ውሀው እስከ ፲፪ ሜትር ይነሳል። የምስር መልክ ፫ ግዜ ለዓመት ይለዋወጣል። ከመስከረም እስከ ጥቅምት ምስር ሁሉ ሐይቅ ይመስላል። በበጋ ዐይን የሚያጸባርቅ፥ የደረሰ ሩዝና ስንዴ የሞላ ይታይሃል። ከመከሩ በኋላ ግን በረሃ ነው የሚመስል።

ከለዚያ አስቀድመው የተጠሩ ሐይቆች ያነን ከሱዳን ያለ ጻድ የሚባል ትልቅ ሐይቅ እናመለክታለን። ወደሱ የሚፈስ ሻሪ ወንዝ ይባላል። ከሱ የሚወጣ ወንዝ እንኳን ባይኖረው ውሀው ጣፋጭ ነው። በክረምት ግዜ እጅግ አድርጎ ከፍ ይላል፥ ዳር ዳሩን ሳር እንደ ታፈነ ነው።

## የአፍሪቃ አየር።

አፍሪቃ ሙቀት የሚሰለጥንበት አገር ነው። ምክንያቱም እንዲህ ነው ቅርብ አፍሪቃ ሁሉ ከመሀከለኛ የምድር ዙርያ አጠገብ ነው፥ የፀሐይ ሙቀት ኃይልም ከዚያ የቆመችበት ሰማይ ከሁሉ ይልቅ ከመሀከለኛ የምድር ዙርያ ነው የሚወድቅ። ከብዙ ስፍራም ያነን አገር እጅግ የሚበቅል ነገር ስለ ሌለበት፥ ለፀሐይ እንደ ክፍት ነው። ላገሩ ባሕር እንዳያበርደው ደሞ፥ ባሕሩ በሰፊው ዓለም ክፍል ውስጥ የማይገባ ሆነ። ያነን ከሰፊዎች የበረሃ አሸዋ የሰለጠነ ሃሩር ደሞ፥ በነፋስ ከለዚያ ባቅራብያቸው ያሉ አገሮች ይደርሳል። ያነን ከሰሃራ የተነሳ የሃሩር ነፋስ ወደ ደቡብ ኤውሮጳ አድርጎ ቢነፍስ ሺሮኮ ይሉታል። ወደ ምዕራብ ከሰኔጋምቢአ አድርጎ ቢነፍስ ሓርማታን፥ ወደ ምስራቅ ከምስር በላይ ቢያልፍም ካምሽን ይሉታል። አንድ መንገደኛ ዓረብ አለ፤ «ከኑቢአ ምድር እንደ ፍም ነፋስ ደሞ እንደ ነበልባል ነው»።

ስለ የአፍሪቃ አየር ሌላ የምናመለክተው ደሞ ይህነን ነው፤ የአፍሪቃ አየር እርጥብና የሌለው ሁኖ፥ ባያሌ ስፍራ ደረቅ ነው። ባያሌ አገሮች ዝናብ እንደ ሚጥል እውነት ነው ግን በሰሃራ በሞላውና በኒል አገሮች አልፎ አልፎ ጥቂት ባይሆን፥ ምንም ዝናብ አይጥልም። ከአፍሪቃ ደቡብ ደሞ ዓመት ሙሉ ዝናም የማይዘንብበት አገር ይገኛል። የሰሃራ አየር ምንጮች የሚደርቅ የእግር ኮት ባሸዋ ቀብሮ የሚያጠፋ ስለ ሆነ ለመንገደኞች እጅግ የሚያስፈራ ነው።

በእርጥብና መጉደል ምክንያት ደሞ ያነን የሚበቅል ዓይነት እንደነዚያ ሌሎች የዓለም ክፍል የሚያህል ብዙ አይዶለም። ዝናብ የሚዘንምበት ያ ከመሀከለኛ የምድር ዙርያ አጠገብ የሚገኝ አገር ብቻ ነው። እርሱ ደሞ ክል የሌለው የሚበቅል ዓይነት ስለ ሞላው ህንድና የአሜሪካ ደቡብን ይመስላል። በንዲህ ያሉ ስፍሮች፥ ለማለፉ እንኳን እጅግ የሚያስቸግር፥ የታጨፈስ ደን ጐርፍ የሚሄድበት ሁሉም ልዩ ልዩ ዓይነት የውሀ ሳር ይሞላል። ከምዕራብ አፍሪቃ ገመገም አጠገብ አንድ ሰፊ፥ ብዙ ሺሕ ኪሎ ሜትር ኳድራት የሚሆን ስፋቱ ጨቀጨቅ የሆነ ሜዳ አለ። በሱ ዓይነት ቅጠል ይበቅልና ተጐናጐኖ እንደ ግምብ ሁኖ ይቆማል። እርሱም ለማየቱ ድንቅ ነው። ያ ከመሀከለኛው የምድር ዙርያ አጠገብ አልፎ ግን ያገሩ መልክ የሚሆነው ሌላ ነው። በሰሃራ ግን ውሀ ስለ ሌለበት የሚበቅል ነገር የለም። በብዙ ኦኣሲ ደሞ ከጠዘዘ እሾህና አካስያ በቀር ሌላ አይበቅልበትም። ደህና ደህና መሬት ግን እህልና ተምር የሚያፈራ ስሌን ይገኛል። ከመሀከለኛው ባሕር ያሉ የአፍሪቃ አገሮች የበለጠ በዛፋቸው ኤውሮጳ ደቡብን ይመስላሉ።

ደቡብ አፍሪቃ በሚበቅል ነገር ድኃ ነው። በዚያ እልፍ እልፍ ብሎ ብቻ ነው ዱር የሚገኝ ሳሩ እንኳን በጋ ሲሆንስ ይደርቃል። ካጽ የተባለ አገር ያበባ አገር ነው። ለሰው ምግብ የሚሆን የሚበቅል ነገር ጥቂት ዓይነት ብቻ ይገኝበታል

ዱርም የለበትም። በተቀረው ግን ያገር ብዙ ዓይነት አታክልትና ሣር ያወጣል በብዙ ዓይነትና ቀለም ያለበት አበባም ይሸለማል። በጋ ሲሆን ግን፥ ሁሉ ይደርቃል።

ቅርብ ሁሉ አፍሪቃ ማሽላ ይሆናል። በካጽ ደሞ የኤውሮጳ እህል መዝራትና ወይን መትከል ይሰላል። ከጉኔኣ ወደ ሌላ አገር የሚሸጥ፥ የስሌን ዘይት ነው። ከሰሜን አፍሪቃ ደሞ ተምርና ላስቲክ፥ ከመሀከለኛ አፍሪቃ ኣኡትሹክ ከካጽ እህልና ወይን፥ ከምስር እህልና ጥጥ ይገኛል።

## የአፍሪቃ እንስሳ።

ከሌሎች ዓለም ክፍል የማይታዩ እንስሶች ከአፍሪቃ ይገኛሉ። ለዚህም ከአዕዋፉ ሰጐን፥ ተንፋዋቀው ከሚሄዱ ደሞ አዞ እናመለከታለን። እንዳንደ ግዜ በአፍሪቃ ደቡብ እስከ ፲ እልፍ የሚያህሉ ሚዳቆች ባንድ ተሰብስበው ይገኛሉ። ዝሆንና ጉማሬ የመሰሉ ያለልክ ናቸው። ከፍሪቃ እንስሳ የሚገኝና ወደ ውጭ አገር የሚሸጥ የበለጠ የሰጐን ላባ የዝሆን ጥርስና ቄደ ናቸው። የቤት እንስሳ እንደ ሌሎች የዓለም ክፍል ያሉ ናቸው። ከነዚያ ቅዝ ያሉ የኮንጎ ሜዳ በቀር ላሞችና እርኩስ ከብት ባፍሪቃ ይገኛሉ። በዚያ ግን እርኩስ ከብትና ላሞች እጅግ አይገኙም። ምክንያቱም ደሞ እነዚያ በዚያ ስፍራ የሚገኙ የከብት መዓት የሆኑ ዝምብ ናቸው። ግመሎች የበለጠ ከአፍሪቃ ሰሜን ናቸው የሚያገለግሉት። ከፍሪቃ ደቡብ በሬ ጋሪ ይጐትታል እንደ በቅሎም ይቀመጡበታል። ግን በዚያ በክፉው ተናካሽ ዝምብ የቤት እንስሳ ይጠፉሉ።

## የአፍሪቃ ሕዝብና መንግሥቶቹ።

የአፍሪቃ ባላገሮች ስንት እንደሆኑ እርግጡን የሚነግር የለም፥ ግን ፪፻፷ ሚልዮን ያህላሉ ናቸው የሚባሉ የአፍሪቃ ባንዳንድ አገር ለም ሕዝብ አለበት፥ አንዳንዱ አገር ግን ሰዉ ጥቂት ነው። እስካሁን ስማቸው ያልታወቀ ሕዝብ ደሞ አሉ። በአፍሪቃ ሰሜን ዓረቦች ጥሰው ገቡ፥ ግን ቋንቋቸውን ለመናገር ባላገሮቹን ግድ አላልዋቸውም ከሳቸው ጋራም ተደባልቀው ቀሩ። ከአፍሪቃ አንዳንድ ነገድ ከሌላ ሳይዛመድ ተለይቶ ይኖር ነበረ፥ አንዳንድ ደሞ ከሌላ ጋራ ተደባልቆ ክልስ ሁኖ ቀረ። ከሰሜን አፍሪቃ ያሉ ሕዝብ ከሴሚቲ ጋራ ይዛመዳሉ። እነዚያ ከሰሜን አፍሪቃ ያሉ ሕዝብ መልካቸው ቢጠቍር ነው እንጅ የለዚያ በደቡብ ምዕራብ እስያ ያሉ ሕዝብ ዘመዶች ናቸው። ብዙ አይሁድም ከሰሜን አፍሪቃ፥ የበለጠ ከመሀከለኛ ባሕር ዳር ተቀምጠዋል። እለዚያ በሰሜን ምሥራቅ ያሉ የኢትዮጵያ ሕዝብም አንድ ጫፍ ነገደ ሴም ናቸው።

ከካም ወገን የሚቈጠሩ የሚከተሉት ናቸው በርበር፥ የነዚያ ከበርበርና ሰሃራ የሚኖሩ ልጆች የጋላ ሕዝብና ሶማሊ። ካቢሊ የተባሉ ከአልጀሪ ማኡሪ ወደ ማሮኮ ከምዕራብ ሰሃራ አቅራብያ። የታኡሬግ ሕዝብ ከበርበር ወገን ናቸው። አለዚያ በፖርቶጌስ ጭከና የጠፉና በካናሪ የተባሉ ደሴቶች የተቀመጡ ከዋሻም የሚኖሩ ጓናጨርኒ የተባሉ እንደ ግብጻውያን ለሬሳ የማያገማ መድኃኒት የሚቀቡ ከበርበር ወገን ናቸው የሚቈጠሩ። ከበርበርም ብዙ ከዓረብ ጋራ የተደባለቁ አሉ። ነጮችም ሞሪ የተባለ ስም አውጥተውላቸዋል። እለዚያ ፲፱ ሽሕ ነፍሳት የሚያህሉ ከምስር ያሉ ኮብት የጥንታውያን ግብጾች ልጆች ናቸው።

ካምቲና ኔግር የተደባለቀበት ነገድም አለ እንደ ኑቢኣ ሕዝብ የቲቡ ሕዝብ ከሰሃራ ምሥራቅ የፈላታ ሕዝብ የሚመስሉም በምዕራብ ሱዳን። የፈላታ ሕዝብ ብልህ ነው የነበረና በሱዳን ሰፊ ቦታ ያዘ አሁን ግን ኃይሉ እየደከመ ይሄዳል።

እነዚህ ኔግር የተባሉ ነገድ ከሰሃራ በደቡብ ያለ አገር ይዘዋል። ኔግር ጥቁሮች ኀይለኞች፥ ገምባራሞች፥ አግጫሞች ከንፈራሞች ራስ ቊንዶ ናቸው። የኔግር ነገድ ስለ መልካቸው ልዩነቱ በሶስት ይከፈላል፤ ከሰሜን የሱዳን ኔግር፥ የባንቱ ኔግር ከኤኳቶር በስተ ደቡብ። ከመሀከላቸው ያሉና ከሁለታቸው የሚዛመዱ እለዚያ ከታችኛ ጕኔኣ የሚኖሩ የኮንጎ ኔግር ናቸው። የፋን ሕዝብ በዳር ከኤኳቶረ ደቡብ ወገን የኛምኛም ሕዝብ ከኒል ምንጭ አጠገብ፥ የማንዲንጎ ሕዝብ በላይኛው ጕኔኣ ያሉ የሱዳን ኔግር ናቸው። ባንቱ ኔግር የተባሉ እንደ የዙኣሄል ሕዝብ፥ ኩናማ፥ ካፍር የመሰሉም ከደቡብ ምሥራቅ

የሆተንቶት ነገድ ቊጥራቸው አያሌ ሺሕ ነው ግን ከኔግር በብዙ ነገር የሚለዩ ስለ ሆኑ፥ ብቻቸው ልዩ ነገድ እንደሆኑ እንቈጥራቸዋለን። የቈርበታቸው መልክ ብጫ ፊታቸው ሰፊ አፍንጫቸው ደፍጣጣ፥ ጠጕራቸው ላሁጫ፥ ቋንቋቸው መብል የሚያጣጥሙ ይመስላሉ፥ ለማያውቀው የሚያስገርም ነው። ከፊት ጀምረው ካጵ አገርን የያዙ እነሱ ናቸው አሁን ግን አገራቸው ነጮች ወርሰውታል። ከካጵ አገር የሚኖሩ ግሪካስ የተባሉ ድብልቅ ከሆላንዲኣና ሆተንቶት የተወለዱ ናቸው። ከፍሪቃ ውስጥ ደሞ ማስተዳደርያቸው አደን የሆነ፥ ቊመታቸው ደሞ አንድ ክንድ ተስንዝር የሚያህል ሕዝብ አሉ፥

## የአፍሪቃ ሕዝብ ሃይማኖት።

የአፍሪቃ ሕዝብ ሃይማኖት ከክርስቲያን እስላምና አረሚ ይከፈላል። አፍሪቃ ሰሜን ሱዳን፥ ከምሥራቅ አፍሪቃ ደሞ ትልቅ ክፍል የእስላም አገር ነው። ከአፍሪቃ የበለጠ ወደ እስልምና ፈጥነው የሚሳቡ እለዚያ የተዋረዱ ሕዝብ ናቸው። በክርስትናቸው ስላልጠነከሩ መንፈሳዊ እውቀትም ስላልነበራቸው እለዚያ በምሥራቅ የሚኖሩ የመንሳዕ ሕዝብ በኤሪትሬኣ ያሉትንም ደሞ እስልምና አሸነፋቸው።

በአፍሪቃ የሚበዙ ሕዝብ አረማውያን ናቸው። አንዳንዱ ጣኦት የሚያመሊ እኵሌቶች ደሞ የሞቱት ሰዎቻቸውን ነፍሳት የሚያመልኩ ናቸው። ከነሳቸው የሰለጠነ የአረሚነት ጨለማ ምክንያት ደሞ ከብዙ ዓይነት ስህተትና ኃጢአት ይመላለሳሉ።

የአፍሪቃ ክርስትያን ገና ጥቂት ናቸው። ከኒል አገሮች አንድ ድብልቅ መሳይ፤ ብቻ አፍአዊ ስራት የሚጠብቅ መንፈሳዊ ኃይል የሌለበት አንድ ዓይነት ክርስትና ነበረ።

ካያሌ ዓመት ጀምሮ የነጮች ማሕበራት ለሕዝብ የሚያስተምሩ ብዙ ሺሕ ሰዎች ይሰዳሉ ብርሃን ጨለማን ያበራል፥ ክርስቲያኖች ደሞ እየበዙ ይሄዳሉ። ቀድሞ ሰው እያረዱ ሲሰዉ የነበሩ ለጣኦታት የሚሰግዱ፥ ለምዉታን መናፍስትም ሲፈሩ የነበሩት እንኳን ሳይቀር፥ አሁን ያነን አንድ አምላክ የሆነ ያመልካሉ። ከክርስትና ጋራም ብርሃን መልካም ስርዓት፥ ጽድቅና ምሕረት ደሞ ተከተለ።

የአፍሪቃ ሕዝብ ትዳር የበለጠ እርሻ፥ ከብት ማርባት አድን ነው። ከግብጽ ሕዝብና ከኑቢአ ሕዝብ በቀር የአፍሪቃ ሰሜን ሕዝብ ዘላኝ ናቸው። በተቀሩ አገሮች ደሞ ያርሳሉ ከብት ያረባሉ ያድናሉ። ያ ሕዝብ ብልሃትን ያልተማረ ስለ ሆነ ደሞ ባገሩ ከሚገኝ ፍሬ እህልና አታክልት በቀር ወደ ሌላ አገር ሂዶ የሚሸጥ እቃ መስራት አይችሉም።

ካያሌ መቶ ዓመት በፊት ባሮች ከአፍሪቃ እየተዙ ወደ ሌላ አገር ይሸጡ ነበሩ፥ እንደ አሜሪካ ደቡብና በአረብ። ስድስተኛ ፍርድሪክ የዳኒማርክ ንጉሥ ግን በለዚያ የሱ ግዛቶች የነበሩን የህንድ ምዕራብ ደሴቶች ባሮች መሸጥ ከለከለ ከዚያ በኋላም እንግሊዛውያን ከለከሉት። ከዚህ ባሮች ማደን የተነሳ ብዙ የኔግር ነገድ ከዓለም ጠፉ፥ ሊበንስግስቶን እንዳለ፥ «ያነን የሚያስደነግጥ፥ የመረረ የአፍሪቃ ቊስል ባርነት ነው።»

በሚከተሉት ክፍሎች ስለ ሕዝቡ፥ ትዳር ቍጥሩ በያገሩ ያለ አገዛዝም ከሰሜን ጀምረን እናመለክታለን።

# የአፍሪቃ አገር ክፍል።

ከመሀከለኛ ባሕር ያሉ አገሮች ማሮኮ አልጀሪ ቱኒስ ትሪፖሊ ብዙ ሕዝብ ከበርበር ነገድ ስለ ተቀመጠበት የበርበር ግዛት ተብሎ ይጠራል። ከባሕር አጠገብ ያለ መሬት ፍሬያም ነው። ያነን አንዳንድ ኦኣስ ወይም ዋዲ ያለበት ሰሃራ ደሞ በደቡብ ወገን ክፍላቸው ነው። ባላገሮቹ የወርቅ አፈር ጎማ፥ የዝሆን ጥርስ ግመሎችን እየጫኑ ይነግዳሉ። ያ አገር ደሞ ከለዚያ ገበሬዎችና እረኞች የሆኑ በርበር በቀር፥ ዓረብና ሞር ተቀምጠውበታል።

## ማሮኮ።

በፈረንሳዊ የሚገዙ ሕዝብ ፭ ሚልዮን ያህላሉ። የማሮኮ ሰዎች የእርሻ አገባብ በጣም የማይችሉና ተጠናክረው የማይዙት ሳሉ፥ ብዙ ስንዴ፥ ገብስ ባቄላም አያከማቹ ይሸጣሉ። ያገራቸው ዋና ከተማ ፻፵ ሺሕ ሰውም ያላት ፌዝ ታባላለች።

## አልጄሪአ።

ያገሩ ስፋት ኢትዮጵያን ያህላል። ሰዎቹ ደሞ ፭ ሚልዮንና ፱፻፶ ሺሕ ናቸው። ከፈረንሳዊ እጅ በታች ከሆኑ ፺ ዓመት አድርገዋል። እርሳቸው የባብር መንገድ አሰርተዋል፥ ለበረሃው አሸዋ ሳይቀር በብልኃት ውሀ ወደሱ መርተው ፍሬያማ መሬት አደረጉት። ያ አገር ብረት ይገኝበታል። ወይን፥ የወይን ፍሬ፥ ትምባሆ የቡሽ፥ እንጨትም ከዚያ አገር ይሸጣል። ዋና ከተማ አልሺር፥ ደሞ ፻፶ ሺሕ ያህላሉ።

## ቱኒስ።

ቱኒስ አገሩ ጠባብ ነው። ሕዝቡ ፪ ሚልዮን ናቸው። ከባሕሩ ዳር ማለፍያ ወደብ አለችበት። በዚያ የትልቂቱ የካርታጎ ከተማ ፍራሾች ይገኛሉ።

## ትሪፖሊ።

ያገሩ ስፋት ከኢትዮጵያ ጥቂት ይጐድላል። ሰዉ ፩ ሚልዮንና ፫፻ ሺሕ ብቻ ናቸው የሚሆኑ። በ፲፱፻፲፪ ዓመት ኢታልያን እስቲወስደው ድረስ፥ በቱሩክ ይገዛ ነበረ። በባሕሩ ዳርዳር ያለው መሬት ፍሬያም፥ ያገሩ ውስጥ ግን በረሃ ነው።

## ምስር።

ምስር ከብዙ ዘመናት ጀምሮ እጅግ የስለጠነ መንግሥት ነበረ። እለዚያ እስካሁን ያሉ የሚያስገርሙ ፍራሾች፥ ስለ ጥንታዊ የምስራውያን ክብረትና ብልህነት ይመስክራሉ። የነዚያ ከካይሮ እጠገብ ያሉ ፒራሚድ ፻፶ ሜትር የሚያህል ነው ርዝመታቸው። ከሉክሶርና ካርናክ መቅደሶች የነበሩ የሚያስደንቁ ትልልቅ ፍራሾች ይገኛሉ። ከካይሮ ከምስር ሙሴዎ ውስጥ እለዝያ ፬ ሺሕ ዓመት ያደረጉ ከፒራሚዲ ተቀብረው የነበሩ ሬሶችና ከምስር በሞላው የተጠራቀሙ ብዙ ዓይነት የቀድሞ ዘመን እቃም ተሰብስበዋል እነዝያ ሙሚ የተባሉ ሬሶች ብዙ ሺሕ ዓመት ተቀምጠው ኑረው ሳሉ ደህና ሳይበላሹ አሉ። በዚህም ምስራውያን የሚያስደንቅ ጥበብ እንደ ነበራቸው ይገለጣል።

አሁን ምስር ፲፬ ሚልዮንና ፪፻፶ ሺሕ ሰው አሉበት የሚበዙትም ከነገደ ዓረብ ናቸው። እርሳቸው በ፯ኛው ዓመት ያነን አገር ያዙት። እለዚያ ኮብት የተባሉ የጥንት ግብጻውያን ልጆች ፰፻ ሺሕ የሚያህሉ ናቸው። ከከተሞች የሚቀመጡ ነጮችም ፻ ሺሕ ያህላሉ። ከለዚህ በቀርም አርመን አይሁድ፥ ሶርያውያንና ቱርክ እልፍ እልፍ ብለው በምስር አገር ይገኛሉ። ከኮብት በቀር ባላገሮቹ እስላም ናቸው። ዋና የእስላም ትምህርት ቤት ባካይሮ ነው። ከዚያ ዓመት ለዓመት ወደ አፍሪቃ የእስልምና ሃይማኖት ለመዘርጋት ተልከው የሚወጡ ብዞች ናቸው። ያች ከኮብት ቤተ ክርስቲያን ሁሉ የምትበልጥና የምትልቅ የኤጲስ ቆጶስ መኖርያም የሆነች ቤተ ክርስቲያን ደሞ በካይሮ ናት ያለች።

የአሜሪካ ወንጌል ማሕበርም ለባላገሮቹ ባያሌ ስፍራ ትምህርት ቤቶችና ቤተ ክርስቲያን ሰርተውላቸዋል።

ምስር በስፋቱ ኢትዮጵያን ይቀርባል፥ የምስር ከተሞች ግን ደህና ሁነው የተሰሩ ትልልቅ ናቸው። በትልቅነትዋና በመድመቅዋ ካይሮን የምታህል ከተማ ከአፍሪቃ በሞላው አትገኝም። ሰዎችዋ ፮፻፶ ሺሕ ናቸው። እስክንድርያ ፫፻፵ ሺሕ ሰዎች አሉባት። በእስክንድርያ ማለፍያ ወደብ አለ። ሱዌስና ፖርቶሳይድ መጠነኞች ከተሞች ናቸው። ፊተኛይቱ ከኤሪትሬኣ በሰሜን ከካናሉ አጠገብ ኋለኛይቱ ከመሀከለኛ ባሕር ከስዌስ ካናል በር። ብዙ ሺሕ መርከቦች ከሞላው ዓለም በዚያ ማለፍ የታቻላቸው የምዕራብና የምሥራቅ ሕዝብ ደሞ ማቋረጫ አግኝተው እርስ በርሳቸው ተቀራርበው ያሉ ይህነን ከበረሃ ተቈፍሮ ያለ፥ ልክ የሌለበት ገንዘብ ያጠፉበት፥ ትልቅና ቅኑ ካናል ስላለ ነው። ካናሉ ያለ በፈረንሳዊና በእንግሊዝ እጅ ነው። ያገሩ ጌቶች ሁነው ያሉ ደሞ እንግሊዛውያን ናቸው። ያነን ባካይሮ ተቀምጦ ያለ ሱልጣን ከእንሊዞች መንግሥት በታች ነው የሚገዛ። የነን ፍሬያም መሬት ዓመት ዓመት የሚያፈራው የብዙ ሺሕ ሚልዮን ነው።

## ሱዳን።

የሱዳን ስፋት ከኢትዮጵያ ሁልት እጅ ነው። ሕዝቦቹ ፮ ሚልዮንና ፰፻ ሺሕ ናቸው እርሳቸውም እስላም ብቻ ናቸው። ላይኛው ክፉ ኑቢኣ ታችኞች ካርዶፋንኒ ዳርፉርኒ ይባላሉ። ከመሬቱ የሚበዛ ፍሬያም ነው። ግን አገሩ ሰፊ ሳለ ሰዎቹ ጥቂቶች ናቸው። በዎንዞቹ ዳርና በቈላው ደሞ ሰው ያልረገጠው ብዙ ዓይነት አውሬና ዝሆን የሚመስሉ እንስሳ የሚገኙበት ትልቅ ዱር አለ። በሱዳን መሬት የበለጠ የሚፈራ ማሽላ ተምር ትምባሆና ኢንዲጎ የተባለ አንድ ሰማያዊ ዓይነት ቀለም የሚወጣበት ተክል ነው። የበለጠ ከሱዳን ናቸው ዓረቦች ብዙ ሺሕ ባላገሮችን እየዘረፉና እየሰረቁ እንደ እንስሳ ሲሸጥዋቸው የነበሩ። ያ አገር እንግሊዝ ከያዙት ግን በባሮች መነገድ ቀረ። የሱዳን ዋና ከተማ ካርቱም ናት። ፖርት ሱዳን ሱዋኪን ደሞ ከባሕሩ ዳር ከነዚያ ባገሩ ውስጥ ያሉ ካርቱምና ዋዲ ሃልፉን በብረት መንገድ ይተባበራሉ።

## የሱማሊ አገር።

የሱማሊ አገር በየክፍሉ ከኢታልያ፥ እንግሊዝና ፈረንሳዊ ግዛት ነው ያለ። ስፋቱ ደሞ የኢትዮጵያን እኵሌታ ያህላል። ከሱማሊ አገር ሰፊ ክፍል የኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት ነው። ወደቡ ያለባቸው ከተሞች የሚከተሉት ናቸው፤ ከፈረንሳዊ ግዛት ጂቡቲ። ያነን ወደ አዲስ አበባ የሚገባ ብረት መንገድም የሚጀምር ከዚያ ነው። ከእንግሊዝ ግዛት በርበራ፥ ከኢታልያ ግዛትም ሞጋዲሾ። ከሕዝቡ የሚበዙት ዘላኝ ናቸው።

ወደ ውጭ አገር የሚሸጥ የንግድ እቃ፤ ከብት፤ የሰጐን ላባ፤ የዝሆን ጥርስ፥ ጎማ ሰምና ቈዳ ነው።

# አፍሪቃ ምሥራቅ።

ያነን በጋላና ሱማሊ እስከ ሮዴስኣንና ትራንስባል ያለ ስፋቱ ፫ ግዜና እኵል ኢትዮጵያን የሚያህል አገር አፍሪቃ ምሥራቅ ይባላል። ያ ላይኛው ከጋላና ሱማል አጠገብ ያለ ክፍል የእንግሊዝ ግዛት ነው። ያ ከሱ ጋራ የሚቈጠር የኡጋንዳ አገርም ስፋቱ ኢትዮጵያን ያህላል። የሕዝቡ ቍጥርም ፫ ሚልዮን ነው። ከቅርብ ዘመን በፊት የኡጋንዳ ሕዝብ ከአረሚነት ጨለማ የሚመላለሱ፥ ለጣዖታት የሚሰግዱ፥ ሰው እያረዱ የሚሰዉ ሕዝብ ነበሩ፥ ግን በወንጌል ማሕበር ስራ ሕዝብ በሞላው ነቅትዋል። እንደገና የጠራ፥ ብርሃን፥ ጥበብና ጽድቅ የሚሰርጽበት ሕዝብ ሁነዋል። የኡጋንዳ ዋና ከተማ መንጎ ትባላለች፥ ከትምህርት ቤቶች በቀርም ፫ ሽሕ የሚያህል ሰው የምትይዝ ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ከከተማው መሀከል ተሰርታለች። ሞምባሳ የተባለች ከተማ ማለፍያ ወደብ አለችባት፥ የነን እስከ ኡጋንዳና ቢክቶርያ ኒያንሳ የተባሉ ሐይቅ የሚደርስ የብረት መንገድ ከዚያ ነው የሚነሳ።

ያ ስፋቱ እርሱን የሚያህል መሀከለኛ ክፍል አስቀድሞ የነምሳ ግዛት የነበረ፥ አሁን ወደ እንግሊዝ አልፍዋል ከነዚያ በስተ ምዕራብ ሰሜን ለኮንጎ ቤልጂክ የሚቀርቡ በቀርም ሩአንዳና አሩንዲ የተባሉ ትንንሽ አገርም ከኮንጎ ቤልጂክ ይቈጠራል። ያ የብረት መንገድ የተጠረገበት ምድር ግን የእግሊዝ ሊባል ነው።

ሕዝቦቹ ፬ ሚልዮን ናቸው። ያች ከባሕር ዳር ያለች ሰፊ ወደብ ያላት ዋና ከተማይቱ ዳር ኤስሰላም ትባላለች። ያነን አገር ሰፊ ዱር አለበት። በነምሳ ማሕበር መልክተኞችም ትልቅ የክርስቲያን ማሕበር ሁኖበታል።

ታችኛው ክፍል የፖርቱጊስ ነው። ሕዝቦቹ ፫ ሚልዮን የሚያህሉ ናቸው። ከለዚያ በፊት ያልናቸው ክፍሎች ጥቂት ያንሳል ግን መሬቱ ፍሬያማ መሬት ነው። የብረት መንገዶች ከሮዴሲአንና ትራንስባል ጀምረው ከለዚያ ሰፊ ወደብ ያለባቸው ከተሞች ይደርሳሉ። ያገሩ ዋና ከተማ ያች በደሴት የተሰራች ሞሳምቢክ የተባለች ናት።

በለዚያ ፫ አገር ክፍል የሚፈራና ትርፉ ወደ ሌላ አገር ሂዶ የሚሸጥ፤ እህል፥ ቡን፥ ሙዝ፥ ባሕር ማሽላ፥ ካካው ዘይትና አኡቹክ ነው የዝሆን ጥርስና እንዲሁ ያለ ሌላም አለ።

# የእንግሊዝ አፍሪቃ ደቡብ።

የእንግሊዝ መንግሥት በአፍሪቃ ይዘዋቸው ያሉ አገር ክፍሎች ስፋታቸው ከ፫ ግዜ ኢትዮጵያ ይበልጣሉ። በዚያ የሚኖሩ ሕዝብ ደሞ ባንድነት ቢቈጠሩ ፯ ሚልዮንና ፮፻፴ ሽሕ ያህላሉ። በየክፍሉም እለዚያ እንግሊዛውያን የሾሙዋቸው አያሌ ያገር ልጆች ሹማምንትና እንግሊዛውያን ሹማምንት ይገዛሉ። እንግሊዞች ግዛታቸው በሆኑት አገር አያሌ ብረት መንገድ አበጅተዋል። ያገሩ ክፍሎች ስም እንደሚከተለው ነው።

## የካፕ አገር።

ሕዝቡ ፪ ሚልዮንና ፫፻፷ ሺሕ ነው። ፬ኛ እጅ ከባላገሮቹ ከነገ ኤውሮጳ የቀሩት ግን ካፍሪቃ ሆተንቶቲ ማላዩ ናቸው። ያ ከባሕሩ ዳር አጠገብ ያለ ሜዳ ፍሬያም ነው። እልፍ ብሎ ግን አገሩ ከፍ እያለ ይሄዳል። ያገሩ አየር ጤናማ ነው። ካገሩ ውስጥና ከሰሜን ወገን ግን ውሀ የሚያንስበት አገር አለ። የሕዝቡ ትዳር ከብት ማርባትና ማረስ ነው። እልፍ እልፍ ብሎም የሰጐን በረት ይገኝበታል። በዚያ የሚዘራ፥ ስንዴ፥ ገብስና የባሕር ማሽላ ነው። በስተ ምዕራብ ደቡብ ወገንም ወይን ይተከልበታል። ከኪምበርሊ የተባለ ያገሩ ዋና ከተማ ደሞ በዓለም ካለ አልማዝ የሚወጣበት ጉድጓድ የሚበልጥና ብዙ አልማዝ የሚገኝበት ስፍራ አለ። መዳብና ደንግያ ከሰልም ከዚያ አገር ወጥቶ ይሸጣል።

የካጳ ዋና ከተማ ካጳ ትባላለች ሰዎችዋም ፻፭ ሺሕ ያህላሉ።

## ሃገረ ባሱቱ።

ሌሎች የማይገቡበት ባላገሮቹ ብቻ የተለየላቸው በስተ ሰሜን ከካጵ ያለ ትንሽ አገር ባሱቱ ይባላል። እርሱ በተራሮች የተለየ፥ የሚታረስ፥ ሳር ያለበት ሜዳ ወይናደጋ ነው። አየሩ ደስ የሚያሰኝ ነው።

## ቤትሹአና።

ያ የላይኛው ክፍል ቤትሹአና ከእንግሊዝ መንግሥት በታች ሳለ፥ ሕዝቦቹ በገዛ ሹሞቻቸው ይገዛሉ።

## ሃገረ አዋምቦ፥ ዳማራ፥ ናማኩኣ።

እለዚህ የጠራናቸው አገሮች እስከ ፲፱፻፲፱ ሐምሳ መንግሥት በታች ኑርው አሁን ግን ከለዚያ በአፍሪቃ ደቡብ ያሉ በእንግሊዝ መንግሥትም የሚገዙ አገሮች ይቈጠራሉ። ያገሩ ስፋት የኢትዮጵያን እኵለታ ያህላል። ግን ሰዎቹ ፻፴ ሺሕ ብቻ ናቸው። እሳቸው አያሌ ወገን ናቸው እንደ ናማኩኣ በደቡብ፥ ዳማራ፥ አዋምቦና ሄሬሮ በሰሜን ሽሖች የሚያህሉ ሆተንቶቲም አሉ። የዝያ አገር አየር ደህና ነው። ደኃ መሬት ስለ ሆነም፥ ያገሩ ትርፍ ጥቂት ነው። ያ አገር ከቤትሹአናና ከውቅያኖስ አትላንቲክ መሀከል ነው የሚገኝ።

## ናታል።

ናታል ፩ ሚልዮንና ፻፲ ሺሕ የሚያህል ሕዝብ ይገኝበታል። ከሳቸው ፺፺ ሺሕ የኤውሮጳ ሰዎች፥ ፻፪ ሺሕ ኩሊ፥ የቀሩት ከ፱፻፲ የሚበልጡ ሱሉ ካፍሪ ናቸው። ከዚያ ጋራ የሚቈጠር የሱሉ አገር ደሞ ፻፹ ሺሕ ነፍሳት አሉበት። እነርሳቸው ከጥንት ጀምረው ኃይለኞች፥ ደፋሮች ጨካኞችም ሕዝብ እንደሆኑ፥ ታውቀዋል። ገና አረማውያን ናቸው ያሉ። ቢሆን ግን ወደ ክርስትና የተሳቡቱ ደሞ አያሌ ሺሕ ናላል፤ ሻሂ፥ ቡን ሱካር አገዳ፥ ጥጥ። በዚይ ደሞ አልማዝ የሚወጣበት ጉድጓድ አለ። ባላገሮቹ ከማረሳቸ ጋራ ከብት ማርባትን ይጨምራሉ።

ያገሩ ዋና ከተማ ፒትር ማሪጽቡርግ፤ ወደቡ ደሞ ፖርት ናታል ይባላል።

## አራንሽ።

ከአራንሽ ጋራ የሚገናኙ በሰሜን ትራንስባል በምዕራብና ደቡብ ሃገረ ካጵ በምሥራቅ ደሞ ባሱቶና ናታል ናቸው። ከ፶ ዓመት በፊት ከኦላንዶች የተመሠረት ሬፑብሊክ ነበረ። በ፲፱፻፪ እንግሊዛውያን ሽረው እጅ አደረጉት። ሕዝቦቹ ከብት አሉባቸው የበለጠ ስራቸው ግን ማረስ ነው። ከዚያ ዕንቍና የደንግያ ከሰል ይሸጣል። ሕዝቡ ፫፻፹፫ ሺሕ ናቸው። ያገሩ ዋና ከተማ ብሉምፎንተን ትባላለች።

## ትራንስባል።

እርሱ ከአራንሽ በላይ ነው አገሩም ከባሕር ሺሕ ሜትር ከፍ ያለ ሜዳ ነው። ከሊምፖፖ አጠገብ ትልቅ ዱርና የሰባ መሬት አለ። እርሱ ግን ንዳድ የበረታበት፤ ተናካሽ ዝምብም የበዛበት ሁኖ ለሰው ሆነ ለእንስሳ መኖርያ ለመሆን አይመችም። በተቀረ ግን ለእርሻ ሆነ ለከብት ለማርባት የተገባ መሬት ነበረ። ዋና ነገር የሆነ ለብዙ ሺሕ ሰዎችም ጥቅምና ሃብት የሚሆን ደሞ፥ ያነን በዝያ የሚገኘ ወርቅና አልማዝ ነው። እንደሱ ያለ አልማዝና ውርቅ የሚወጣበት ስፍራ አድርጎ ትርፍ የሚገኝበት በሞላው ዓለም የለም። መቶ የሚያህሉ የስራ ማሕበር (ሶሲኤቴ) በዚያ ይሰራሉ በቀን የ፻፳ ሺሕ ብር ዋጋ የሚያህል ወርቅ ቈፍረው ያወጣሉ። ዓመት ለዓመትም ከዚያ ፻፴ ሚልዮን ብር ያገኛሉ።

ወርቅ የሚገኝበት የበለጠ በዚያች የ፻፳፱ የሆን ቍጥራቸው ሰዎች ያሉባት፥ ዮሐንስቡግ የተባለች ከተማ ናት። አልማዝ የሚገኝበትም የበለጠ ከፕሬቶሪኣ የተባለች ያገሩ ዋና ከተማ አጠገብ ነው። በዚያ አገር ደሞ የደንግያ ክሰልና ብር ይገኛል። በዚያ አገር ይሚኖሩ፥ ልዩ አገር የተጠራቀሙ ፫፻ የሚያህሉ ነጮች፥ ፯ ሚልዮን ከሱሉ ነገድ ቤሹኣና፥ ማካቴ፥ ባሱቶ፥ ፺ ሺሕ ደሞ ኪኑኣ ናቸው።

ከትራንስባል በስተ ደቡብ ስፋቱ ትግሬን የሚያህል ስዋሲ የሚባል አገር ይገኛል። ሕዝቡ ፹፯ ሺሕ ያህላሉ። የእንግሊዝ ግዛትም ናቸው።

## ሮዴሲኣ።

ሮዴሲኣ ከኢትዮጵያ ይሰፋል፤ ሰዎቹ ግን ፯ ሚልዮንና ፬፻ ሺሕ ናቸው። ምንም እንኳን እንደ የትራንስባል የሚያህል ወርቅና አልማዝ ባይሞላው፥ በሌላ ነገር ብሩክ ሃብታም፥ ፍሬያም፥  የብረት፥ ረገድም የሚገኝበት ምድር ነው። ሮዴሲኣ በዚያ በሱ የሚያልፍ የሳምሴሲ ወንዝ በሁለት ይከፈላል። ታችኛው ክፍል የማታቤሊና ማሾና አገር አለበት። አየሩ ደህና ነው። ባገሩ እንደ ዋኖች ሁነው ያሉም የእንግሊዝ ማሕበር (ኩባንያ) ናቸው። የሮዴሲኣ አገር ዋና ከተማ ሳሊስቡሪ ትባላለች።

## ኒያንሳ።

ይህ አገር ስፋቱ ቤጌምድርና ደምብያን ያህላል። የኒያንሳ የትልቁ ሐይቅ ዳርም ነው። ገዮቹ የእንግሊዝ ናቸው። ሕዝቡ ደሞ ፯ ሚልዮን ያህላሉ። ዋና ከተማው ጸምባ ይባላል። በብላንተይር የተባለች ከተማ የወንጌል ማሕበር ትልቅ ትምህርት ቤት ሰርታለች። ከዚያ አገር የሚሸጥ ቡን፥ ሩዝ፥ ትምባኾ፥ ጥጥ ነው።

## <u>አንጎላ።</u>

ከፖርቶጌስ በታች ያለ አንጎላ የተባለ አገር ስፋት ኢትዮጵያን ያህላል። ሰዎቹም ፬ ሚልዮን የሚያህሉ ናቸው። ካገሩ መሀከል ያለ ደጋ መልካም አየርና ፍሬያም መሬት አለበት። ግን እንደሚገባ አልታረሰም። የዚያ መሬት ፍሬ እንደ አፍሪቃ ደቡብ ያሉ አገሮች የሚመስል ነው። ያች ከውቅያኖስ አትላንቲክ ያለች ሎኣንዳ የተባለች የንግድ ከተማ ያገር ዋና ከተማ ደሞ ናት።

## <u>ኮንጎ።</u>

ኮንጎ ስፋቱ ፫ ኢትዮጵያን የሚያህል ትልቅ አገር ነው። በሁለት ትልልቅ ክፍሎችም ይከፈላል ታችኛው ከበልጂክ በታች ተገዝትዋል፥ በሰሜን ምዕራብ ያለ ክፍል ደሞ የፈረንሳዊ ግዛት ነው።

የበልጂክ ኮንጎ በምሥራቅ ወገን ለአልቤርት ንያንሳ፥ ኪዮ፥ ታንጋንጂካና ሙኤሮ የተባሉ ሐይቆች የሚነካ ነው። የኮንጎ ወንዝም ውሀው ከነዚህ ሐይቆች ነው የሚቀበል። እነዚያ ፲፫ ሚልዮን የሚያህሉ ባላገሮች ከባንቱ ወገን ናቸውና፥ የኮንጎ ኔግር ይልዋቸዋል። በአሩዊሚ የተባሉ ከኮንጎ ወንዝ አጠገብ ያሉ ሰፊ ዱሮች ፒግሚ የሚባሉ ብዙ አሕዛብ ተቀምጠዋል። በስተ ስሜን ምሥራቅ ወገን ገና እስካሁን አንዳንድ ግዜ ባሮች የሚያድኑ ዓረቦች ምሥጢር እያደረጉ ይገባሉ።

የኮንጎ አየር ለሰዉ፥ የበለጠ ላልለመዱት ነጮች የሚገድል ክፉ አየር ነው። ከነዚያ ሃሩር የሚበረታቸው ሜዶች ውሀ ጎርፎ የማይሄድ፥ በዚያ ቊሞ የሚኖር ስለ ሆነ ደሞ፥ ንዳድ ይነሳበታል። ያገሩ እኩሌታ ሰው የማያሳልፍ ዱር የሞላው ነው።

ያገሩ ዋና ከተማ ፒትር ማሪጽቡርግ ወደቡ ደሞ ፖርት ናታል ይባላል።

## <u>ኦራንሽ።</u>

ከኦራንሽ ጋራ የሚገናኙ በሰሜን ትራንስባል በምዕራብና ደቡብም ሃገረ ካጵ በምሥራቅ ደሞ ባሱቶና ናታል ናቸው። ከ፻ ዓመት በፊት ከኦላንዶች የተመሰረተ ሬፑብሊክ ነበረ። በ፲፱፻፪ እንግሊዛውያን ሸረው እጅ አደረጉት። ሕዝቦቹ ከብት አሉባቸው፥ የበለጠ ስራቸው ግን ማረስ ነው። ከዚያ ዕንቊና የደንግያ ከሰል ይሸጣል። ሕዝቡ ፫፻፹፫ ሺሕ ናቸው። ያገሩ ዋና ከተማ ብሉምፎንተን ትባላለች።

## <u>ትራንስባል።</u>

እርሱ ከኦራንሽ በላይ ነው አገሩም ከባሕር ሺሕ ሜትር ከፍ ያለ ሜዳ ነው። ከሊምፖፖ አጠገብ ትልቅ ዱርና የሰባ መሬት አለ። እርሱ ግን ንዳድ የበረታበት፥ ተናካሽ ዝምብም የበዛበት ሁኖ ለሰው ሆነ ለእንስሳ መኖሪያ ለመሆን አይመችም። በተቀረ ግን ለእርሻ ሆነ ከብት ለማርባት የተገባ መሬት ነበረ። ዋና ነገር የሆነ ለብዙ ሺሕ ሰዎችም ጥቅምና ሃብት የሚሆን ደሞ ያነን በዝያ የሚገኝ ወርቅና አልማዝ ነው። እንደሱ ያለ አልማዝና ወርቅ የሚወጣበት ስፍራ አድርጎ ትርፍ የሚገኝበት በሞላው ዓለም የለም። መቶ የሚያህሉ የስራ ማሕበር (ሶሲኤቴ) በዚያ ይሰራሉና በቀን የ፻፳ ሺሕ ብር ዋጋ ያሚያህል ወርቅ ቈፍረው ያወጣሉ። ዓመት ለዓመትም ከዚያ ፻፶ ሚልዮን ብር ያገኛሉ።

ወርቅ የሚገኝበት የበለጠ በዚያች ፻፳፱ የሆነ ቍጥራቸው ሰዎች ያሉባት፥ ዮሐንስቡርግ የተባለች ከተማ ናት። አልማዝ የሚገኝበትም የበለጠ ከፐሬቶሪአ የተባለች ያገሩ ዋና ከተማ አጠገብ ነው። በዚያ አገር ደሞ የደንግያ ክሰልና ብር ይገኛል። በዚያ አገር የሚኖሩ፥ ከልዩ ልዩ አገር የተጠራቀሙ ፫፻ ሺሕ የሚያህሉ ነጮች ፩ ሚልዮን ከሱሉ ነገድ ቤሹአና ማካቴ፥ ባሱቶ ፺ ሺሕ ደሞ ኩኑአ ናቸው።

ከትራንስባል በስተ ደቡብ ስፋቱ ትግሬን የሚያህል ስዋሲ የሚባል አገር ይገኛል። ሕዝቡ ፹፯ ሺሕ ያህላሉ። የእንግሊዝ ግዛትም ናቸው።

## ሮዴሲአ።

ሮዲሲአ ከኢትዮጵያ ይሰፋል፥ ሰዎቹ ግን ፩ ሚልዮንና ፬፻ ሺሕ ናቸው። ምንም እንኳን እንደ የትራንስባል የሚያህል ወርቅና አልማዝ ባይሞላው፥ በሌላ ነገር ብሩክ ሃብታም፥ ፍሬያማ የብረት ረገድም የሚገኝበት ምድር ነው። ሮዴሲአ በዚያ በሱ የሚያልፍ የሳምቤሲ ወንዝ በሁለት ይከፈላል። ታችኛው ክፍል የማታቤሊና ማሾና አገር አለበት። አየሩ ደህና ነው። ባገሩ እንደ ዋኖች ሁነው ያሉም የእንግሊዝ ማሕበር (ኩባንያ) ናቸው። የሮዴሲአ አገር ዋና ከተማ ሳሊስቡሪ ትባላለች።

## ኒያንሳ።

ይህ አገር ስፋቱ ቤጌምድርና ደምብያን ያህላል። የኒያንሳ የትልቁ ሐይቅ ዳርም ነው። ገዦቹ እንግሊዝ ናቸው። ሕዝቡ ደሞ ፪ ሚልዮን ያህላሉ። ዋና ከተማው ጾምባ ይባላል። በብላንተይር የተባለች ከተማ የወንጌል ማሕበር ትልቅ ትምርህት ቤት ሰርታለች። ከዚያ አገር የሚሸጥ ቡን፥ ሩዝ፥ ትምባኾ፥ ጥጥ ነው።

## አንጎላ።

ከፖርቶጌስ በታች ያለ አንጎላ የተባለ አገር ስፋት ኢትዮጵያን ያህላል። ሰዎቹም ፬ ሚልዮን የሚህሉ ናቸው። ካገሩ መሀከል ያለ ደጋ መልካም አየርና ፍሬያማ መሬት አለበት። ግን እንደሚገባ አልታረሰም። የዚያ መሬት ፍሬ እንደ አፍሪቃ ደቡብ ያሉ አገሮች የሚመስል ነው። ያች ከውቅያኖስ አትላንቲክ ያለች ሎአንዳ የተባለች የንግድ ከተማ ያገር ዋና ከተማ ደሞ ናት።

## ኮንጎ።

ኮንጎ ስፋቱ ፫ ኢትዮጵያን የሚያህል ትልቅ አገር ነው። በሁለት ትልልቅ ክፍሎችም ይከፈላል፤ ታችኛው ከበልጂክ በታች ተገዝትዋል በሰሜን ምዕራብ ያለ ክፍል ደሞ የፈረንሳዊ ግዛት ነው።

የበልጂክ ኮንጎ በምሥራቅ ወገን ለአልቤርት ንያንሳ፥ ኪዮ፥ ታንጋንጂካና ሙኤሮ የተባሉ ሐይቆች የሚነካ ነው። የኮንጎ ወንዝም ውሀው ከነዚህ ሐይቆች ነው የሚቀበል። እነዚያ ፲፫ ሚልዮን የሚያህሉ ባላገሮች ከባንቱ ወገን ናቸውና፥ የኮንጎ ኔግር ይልዋቸዋል። በአሩዋሚ የተባሉ ከኮንጎ ወንዝ አጠገብ ያሉ ሰፊ ዱሮች ፒግሚ የሚባሉ ብዙ አሕዛብ ተቀምጠዋል። በስተ ሰሜን ምሥራቅ ወገን ገና እስካሁን አንዳንድ ግዜ ባሮች የሚያድኑ ዓረቦች ምሥጢር እያደረጉ ይገባሉ።

የኮንጎ አየር ለሰዉ፥ የበለጠ ላልለመዱት ነጮችን የሚገድል ክፉ አየር ነው። ከነዚያ ሃሩር የሚበረታታቸው ሜዶች ውሀ ጎርፎ የማይሄ በዚያ ቍሞ የሚኖር ስለ ሆነ ደሞ ንዳድ ይነሳበታል። ያገሩ እኩሌታ ሰው የማያሳልፍ ዱር የሞላው ነው። ከኮንጎ ከወንዙ ግራና ቀኝ፥ የሰው እግር ረግጦት የማያውቅ ችፍግ ዱር አለ። በዚአይም ጎማ የሚወጣባቸው ዛፎች ይገኛሉ። በዚያ አገር ቡን እንደ የበረሃ ዛፍ ነው። ብዙ ፍሬ የሚሰጥ ያታክልት ዛፍም እንደ በረሃ ዛፍ ሁኖ ይገኛል። የሱካር አገዳ ሙዝና ናርጌም ሞልቶ ይገኝበታል። ባላገሮቹ ደሞ ሰሌን በጥተው ወተቱን አጠራቅመው አፍልተው ይጠጣሉ። እርሱም የሚያሰክር መጠጥ ነው። ከዚያ አገር ወደ ውጭ ሂዶ የሚሸጥ እቃ፥ የበለጠ የዝሆን ጥርስ ኣኩትሹክ ጎማ፥ ኮፓል (ለቀለም የሚሆን) ለውዝ ካካዎ ቀመም፥ ሩዝ የሰሌን ዘይትም የመሰለ ነው፡

ባርና ቦማ ማታዲ የተባሉ ከተሞችም ከወንዙ አጠገብ ተሰርተዋል። ከነሳቸውም የመንግሥት ከተማ ቦማ ነው።

የፈረንሳዊ ኮንጎ ከብልጅክ ኮንጎ ጥቂት ያንሳል። እኒህ ሁለት ክፍሎች በብዙ ነገር ይመሳሰላሉ። ያነን ላይኛው ዳርቻው እስከ ሱዳን ይደርሳል። ሕዝቦቹም ፲ ሚልዮን ናቸው። ባላገሮቹ ከባንቱ ወገን ናቸው፥ እንደ እንጋቡሴኒ ከባሕሩ ዳር አጠገብ ባተኪ በዚያ ወደ ኮንጎ ወንዝ አዘቅዝቆ የሚወስድ ሜዳ፥ ግን ከሳቸው የሚበዙ እነዚያ በሰሜን ክፍል ተቀምጠው ያሉ ፉንስ የተባሉ ሰው የሚበሉ ናቸው።

ሰፊ ወደብ ያለባት ንግድ የበዛት ቤተ መንግሥት ተሰርቶባት ያለ ዋና ከተማ ሊብርቢል ትባላለች። ኦግዌ የተባለ ወንዝ ከደጋው ያለ ሜዳ ተነስቶ ባገሩ መሀከል አድርጎ በታችኛው አገር ክፍል አልፎ ከባሕር ይፈሳል። ከወንዙ መጨረሻም ሰፊ ዴልታ አለ።

ካያሌ ዓመታት ጀምሮም ከኮንጎ አረማውያን መሀከል የወንጌል መልክተኞች ከኤውሮጳ ወጥተው በዚያ የተነሳም ብዙ ሽሕ ክርስትያኖች ሁነዋል። ለሕዝቡ ደሞ ወደ ጽድቅ የሚመራ ብርሃን ገብቶባቸዋል።

## ካሜሩን።

ይህ አገር ስፋቱ የኢትዮጵያን ሲሶ ያህላል። ሕዝቡ ቍጥራቸው ፫ ሚልዮን ነው። በደቡብ ከኮንጎ ጋራ በሰሜን ከሐይቀ ጫድ ጋራ ይገናኛል። በፊት የነምሳ ግዛት ነበረ፥ ከጦርነት በኋላ ግን ከፈረንሳዊ በታች ሆነ። የበለጠ በዚያ በባሕር ዳር ያለ አገር ሁሉ ዓይነት ፍሬ የሚያፈራ መሬት ነው። ያነን ልክ የሌለበት እሳት የሚይወጣ ከሩቅ የሚታይ፥ እንደ አንድ ትልቅ ፒራሚድ ሁኖ እስከ ፭ ሽሕ ሜትር ወደ ላይ ከፍ የሚል ተራራ ደሞ ከገመገሙ አጠገብ ነው ያለ። ስሙም ካሜሩን ሾላላ ነው። ከተራሮች በላይ የተሰራች ያገሩ ዋና ከተማ ደሞ ቡኤኣ ትባላለች።

## ጊኔሪኣ፡

ጊኔሪኣ ስፋቱ ኢትዮጵያን የሚያህል፥ ሕዝቡ ብዙ ሃብታም አገር ነው። እነዚያ ካያሌ ነገድ የሆነ ባልገሮች እስከ ፲፰ ሚልዮን ነው ቍጥራቸው። ኒጌሪኣ ካንዲት ከእንግሊዝ በታች የምትገዛ ኩባንያ ኒጌር ከምትባል የንግድ ማሕበር እጅ ነው። ከእንግሊዝ መንግሥት ስልታን በታች ሳሉ፥ በባላገሮቻቸው ሹሞች የሚገዙም አያሌ መንግሥታት አሉ። ከነዚህ ሁሉ የሚሰለጥንና የሚሰፋ የለኮቶ መንግሥት ነው። እለዚያ ታናናሾች መንግሥታት፥ አዳማ፥ ጋንዶ፥ በርጉ ኑጵ የተባሉም ላሶኮቶ ገባሩ ናቸው። ያነን ኤሚር የተባለ በሶኮቶ ነግሦ ያለ እስላም ከዚያ ከጥንት የቈየ የገገሮች ነገድ ነው። አሁንም በሱ ላለች ማሕበር ፈቃድ ንጉሥ ሁኖ በምሉ ስልጣን ይዳኛል ይገዛልም።

ከዚያ በታች ወገንም ታናናሾች መንግሥታት አሉ። እርሳችውም አስቀድመው እርሱ በርሳችወ እየተዋጉ ይፋጁ ነበሩ። አሁን ግን ከሚጠብቃቸው የእተዋጉ ይፋጁ ነበሩ። አሁን ግን ከሚጠብቃቸው የእንግሊዝ መንግሥትና ከነዚያ

በሱ የሚያስተምሩ የወንጌል መልእክተኞች የተነሳ ሰላም አግኝተው እየለሙ ይኼዳሉ። የበለጠ የሕዝቡ ትዳር እርሻ ነው። ባገሩ በሞላው ያለ ፍሬያም መሬት ብዙ ዓይነት እህልና ያታክልት ፍሬ ይገኝበታል። ወደ ውጭ አገር ሂዶ የሚሸጥ የበለጠ የሰሌን ዘይት፥ የሰሌን ፍሬ፥ ጥጥ ቡናና አስቀድመን ከአፍሪቃ ወደ ውጭ አገር ሂዶ የሚሸጥ ያልነው ሁሉ ነው። ለዚያ ባላገሮቹ የሚሸጡት፥ በየዓይነቱ ፍሬ የሚያመላልሱ ፺ ትልልቅ የዚያች ማሕበር መርከቦች ደሞ ከጊገርና ቤኑን ወንዞች ይመላለሳሉ። ከላጎስ የምትባል ከተማ ቅርብ ከሁሉ ዓለም መርከቦች ይመጡና፥ ለባላገሮቹ የሚያስፈልጋቸውን ይዘውላቸው ይመጣሉ በዚህ ፈንታ ደሞ ያገሩን ፍሬ ይወስዳሉ። ከአፍሪቃ ምዕራብ እንደ ላጎስ ያለች ትልቅና የተጠራች ከተማ የለም። በስዋ ያለ ፺፪ ሺሕ ከብዙ ዓይነት የተጠራቀመ ሕዝብ ነው። አስቀድሞ ብዙ ሺሕ ባሮች የሚሸጡበት ገበያ ነበረ። ሌሎች ትልልቅ ከተሞችም እንደነካሰ ከኒገር ዳር አሳባ ካገሩ ውስጥ ከኒገር አጠገብ ካኖ በስሜን፥ ከባላገር ከዴልታው አሉ። ኒገር ከዳሩ አጠገብ ሲደርስ ሳለ፥ ከብዙ ጫፍ ይከፋፈልና፥ ለኒገሪኣ ደቡብ በሞላው ይበተናል።

ከነዚያ ብዙ ነገድ የሆኑ የኒጌሪኣ ሕዝብ፥ እኒያ ከቦርኑ የሚኖሩ ያሉ ካኑሪ ኔግሪ እናመለክታለን። እነርሳቸው ከአፍሪቃ ምዕራብ ሕዝብ ሁሉ ፈጣኖችና ብልሆች በመሆናቸው ታውቀዋል።

# የእንግሊዝ ግዛት ከአፍሪቃ ምዕራብ።

እርሳችው ኮት ዶር (የወርቅ ዳር) ሴራ ሌኦንና ጋምቤኣ ናቸው። እኒህ በአየር ሆነ በመሬት እርሱ በርሳቸው ይመሳሰላሉ።

የወርቅ ዳር የተባለ አገር በስተ ደቡብ ውቅያኖስ አትላንቲክን የሚነካ ነው። ያ አገር ብዙ ዓይነት ሃብት አለብት፥ ካገሩ ውስጥ ፍሬያማ መሬትና ዱር ወርቅም ደሞ ይገኛል። ብርቱ ንዳድ ስላለበት ግን፥ የሚገዙበት ጥቂቶቹ ናቸው። በዳር ያለ አገር ፋንቲ ኔግሪ፥ ከሱ በስተ ላይ ያለ ክፍል አሳንቲ ኔግሪ ተቀምጠውበታል። እነርሳቸው በፊት የሚያስፈሩና ተዋጊ ሕዝብ ነበሩ። ነገሥታታቸውን ለባላገሮቹ እስከ ሞት እየቀጡ ላገር በደምና በልቅሶ እየሞሉት በጭከናቸው ምክንያት በዚያ አገር አምባጋሮ ተነሳ ከዚያ በኋላም ያነን ሕዝብ እንግሊዞችን ገዙት። ሕዝቡ ፩ ሚልዮን ተእኩል ያህላል። ዋና ከተማውም ኩማሳ ትባላለች።

ሴራ ሌዎን በምዕራብ ገመገም ከሊቤሪያ አጠገብ ነው የሚገኝ። ሕዝቡ ፩ ሚልዮን ያህላሉ። ከዚያ ያሉ ኔግሪ ፵ ሺሕ ክርስቲያን ፕሮቴስታንት ፯ ሺሕ እስላም፥ የቀሩቱ ግን አረማውያን ናቸው። በፍሪታውንና (ማለት ያርነት ከተማ) በፉራቤ ትልልቅ ትምህርት ቤቶች አሉ።

ያ አገር ለማየቱ ደስ የሚል አገር ነው። አየሩ ግን መርዝ የተረጨበት ነው። ስለዚህም ላገሩ የነጮች መቃብር አወጡለት። ያነን መሬት የፈለጉትን ፍሬ የሚያፈራ ሳለ፥ የሚያርሱ ጥቂቶች ናቸው። በዚህ ምክንያትም ምግብ የሚሆን ከነጮች አገር ያመጣሉ። በዚያ አገር ከማረስ መንገድ ይቀናቸዋል። ለዚያ ባገሩ የሚገኝ ፍሬ ሸጠው በፋንታው ለትዳራቸው ሌላ ነገር ይገዛሉ ፡

ገምቢአ ከሴራ ሌዎን በላይ ያለ ፩፻፷፬ ሺሕ ሕዝብ የያዘ ጠባብ አገር ነው። ከሱ ጋራ የሚቈጠሩ ደሴቶችም አሉ።

## ሊቤርያ።

ስሙ ያርነት አገር ማለት ነው። ያለበት ስፍራ ከባሕሩ ዳር ከሴራ ሌዎን አጠገብ ነው። ግዛቱ ሬፑብሊክ ነው። ሕዝቦቹ ፪ ሚልዮን የሚያህሉ አርነት የወጡ ባሮች ናቸው። በፈረንጆች አገር በመንግሥት ሕግ ባርነት ከተከለከለ

በኋላ፥ የበለጠ በደቡብ አሜሪካ አእላፋት ባሮች አርነት ወጡ በዚያን ግዜ ደሞ አርነት ለወጡት የሚሆን አገር ተፈቅዶላቸው ነበረ። ከ፲፰፻፳፪ አርነት ለወጡ ባሮች ሸሽተው እንደሚጠጉበት ገዳም ነበረ፥ ግን ፲፰፻፵፯ በሥርዓት እንደ ተመሠረተ ግዛት ሆነ። የመንግሥታቸው ሥርዓት እንደ አሜሪካ ነው። እነዚያ ኔግር ለተወሰነ ግዜ አንድ የወንድማማች ሹም ይመርጣሉ እርሱ ከለዚያ ሁለት ክፍል አማካሪዎች ይማከራል፥ በተቀረ ግን ከወንድሞቹ በላይ ምሉ ስልጣን አለበት። ባገሩ አገዛዝ የሚያግዙም ነጮች ሹማምንት አሉ። በዚያ አገር ነጮች ትንሽ፥ መሬትም እንዳይወስዱ በዚያ ፈረንጅ መንግሥታት በገዛጃቸው ያቆሙት ሕግ የተከለከለከለ ነው።

ከነዝያ አርነት የወጡት ለስራ ፈጣኖች የሚባሉ ከክሩመን ነገድ ናቸው እርሳቸው ከባዕድ አገር ሒደው፥ እያገለገሉ ገንዘብ አጠራቅመው ካገራቸው ተመልሰው በዚያ ባተረፉት ገንዘባቸው ያድራሉ። አገራቸው ደሞ ደግና ፍሬያም ነው፡

የሊቤርያ ዋና ከተማ ሞንሮፍያ ትባላለች።

## የፈረንሳዊ ግዛት በአፍሪቃ። ምዕራብ።

የፈረንሳዊ መንግሥት ከአፍሪቃ ምዕራብ ሰፊ አገር ይዝዋል። ያነን ከባሕሩ ዳር ጀምሮ በስተ ስሜኑ ከሰሃራ የሚገናኝ እስከ ኒገሪአ የሚደርስ፥ አገር ከኢትዮጵያ የሚሰፋ ነው። እርሱም ሰኔጋል፥ ላይኛው ሴኔጋልና ጊኔር፥ የፈረንሳዊ ጕኔአ፥ የዝሆን ዳርና ዳሆሜ ነው። እነዚያ ውሀ የሚገኙባቸው ስፍሮች ፍሬያሞች ናቸው። ግን አየሩ ጤናማ አይዶለም። ከአገሩ ዳር አጠገብ የሚቀመጡ ባላገሮች ከዮፍሎስ ነገድ ካገሩ ውስጥ የሚቀመጡ ከነገደ ማንዲንጎ ኔግሪ፥ ከሰሃራ አጠገብ ፉላ፥ ሞሪና ዓረብ ናቸው። ያች ከሰኔጋል ወንዝ ዳር የተሰራች ዋና ከተማዪቱ ሰን ሉዊ ትባላለች።

ዳሆሜ በፊት በጨካኞች ነገሥታት ያገር ልጆች ይገዛ ነበረ፥ እርሳቸው እንደነሱ ያሉ ጨካኞች፥ ጕራዴ የታጠቁ ጠበንጃ የያዙ ተዋጊዎች ወታደር የሆኑ ሴቶች ነበርዋቸው። ሴቶቹ ወደ ጦር ይኼዱ፥ በዚያ ደሞ የሚያስደንቅ ድፍረት ያሳዩ ነበር። ከእጃቸው የወደቀም ለጥፋቱ ነው የነበረ። ዋና ከተማዪቱ ፖርት ኑፎ ናት። ከነዚህ የመለከትናቸው አገሮች ከባሕር ወደ አገሮች ውስጥ የሚያስገባ የብረት መንገድ ተጠርገዋል።

## የፖርቶጌስ ጕኔኣና የስፓኛ ሰሃራ።

ይህ ፊተኛው ትንሽ በሴኔጋልም የተከበበ ኔግር የሚጠቅሙት አገር ነው። የሚቀመጡት አገር ነው።

ከስፓኛ በታች ያለ ሰሃራ ከማሮኮ ጀምሮ እስከ ነጭ ካጵ ይደርሳል።

### <u>ጭማሬ።</u>

በለዚ የጻፍነባቸው ክፍሎች ስለ አፍሪቃን አገሮች ስናመለክት ሳለን፥ ከእገሌ ስልጣን ቤቶች ብለናል። ግን ከነዝያ በፈረንጆች ተገዝተው ያሉ አገሮችም ቢሆን አያሌ የራሳቸው መንግሥት የሆኑ አገሮችና ሕዝቦች ይገኛሉ። ከነዚያ በላይ ስልጣን ያለውም የወንድማማች ሹም ነው። እነዚህም የበለጡ የሚገኙ ባገሮቹ ውስጥ ናቸው። ከለዚህ በወንድማማች ሹም የሚገዙ የሰለጠኑና ትልልቅ የሆኑ እነዚያ ከሻድ ሐይቅ አጠገብ ያሉ ግዛት ናቸው። ስማቸውም ዋዳይ ባጊርሚ ቦርኑ ይባላል።

## ደሴቶች።

ማዳጋስካር የተባለ ከውቅያኖስ ህንድ ያለ ከአፍሪቃ በሞዛምቢክ ካናል የተለየ ከአፍሪቃ በስተ ደቡብ ያለ አገር ነው። እርሱን የሚያህሉ ደሴቶች በዓለም ፫ ብቻ ይገኛሉ። ገዦቹ ፈረንሶች ናቸው። ርዝመቱ ፲፰፻፶፪ ኪሎ ሜትር ሕዝቡ ፫ ሚልዮን ነው። ስፋቱ ከኢትዮጵያን እኵሌታ ይበልጣል። ማዳጋስካር ከአፍሪቃ የሚያፈራ ሁሉ ዓይነት ፍሬ የሚያፈራ፤ ጤናማ አየር ያለበት ማለፍያ ገነትም የሆነ አገር ነው። ከሰሜን ጀምሮ እስከ ደቡብ የሚዞር የተራሮች ጠረፍም ካገር ውስጥ አለበት። ከዚያም መርከቦችን እስከ አገር ውስጥ የሚያሳልፉ ወንዞች አሉ። በዚያን አገር ወርቅ ብር፥ ብረት መደብና እንዲሁ ያለ ሌላ ዓይነትም፥ ይገኛል። ባላገሮቹ ካያሌ ነገድ ናቸው እንደነ ማላጋሲ ሆባስ፥ ሳካላባስ የመሰሉም። ከ፷ ዓመት በፊት ሕዝቡ በሞላው አረሚ ነበረ። ራናባሎና የተባለች ንግሥት ስትነግሥ ሳለች ለክርስቲያኖች ብርቱ ስደት ሆነ እነዚያ በሱ የነበሩት ፈረንጆች መልእክተኞች ተባረሩ፥ ያገር ልጆች ክርስቲያኖችም ጭንቅና መከራ አገኙ አንዳንድ ስለ ሃይማኖታቸው ገደል ጣሉዋቸው አንዳንድም በሌላ አመዋወት ሞቱ። ያ ስደት ጸጥ ካለ በኋላ፥ ወንጌል እየበረታ ሔደ። አሁንም ያገሩ ሃይማኖት ክርስትና ሁነዋል። አያሌ ቤተ ክርስቲያኖች ትምህርት ቤቶች ተሰርተዋል፥ ሺሕ ያገር ልጆች ካህናትም አሉ።

የማዳጋስካር ዋና ከተማ አንታናናሪፍ ትባላለች። ትንንሽ ደሴቶች ማኡሪቱስ ደሴት ከማዳጋስካር በስተ ደቡብ በህንድ ውቅያኖስ ያለ የእንግሊዝ ግዛት ነው። ዋና ከተማዪቱ ፖርት ሉዊ ትባላለች። ባጠገቡም ሬኡንዮን የተባለ ደሴት ከዴኒ የተባለ ዋና ከተማው ጋራ አለ። ከአፍሪቃ ምሥራቅ ዳር ያለ ዛንዚባር የተባለ የእንግሊዝ ግዛት ነው። ደሞ ከሶማሊ ዳር አጠገብ ሶኮትራ የተባለ የእንግሊዝ ደሴት አለ። ኢታልያን የሚገዝዋቸው ደሃላክ የተባሉ ደሴቶችም በኤርትራ ባሕር ከምጥዋ አጠገብ ይገኛሉ። በአትላንቲክ ሰሜን ያሉ ካናሪ የተባሉ ደሴቶች የስፓኛ ግዛት ናቸው፥ ዋና ከተማቸው ደሞ ሰን ክሩ ትባላለች። በታቻቸውም ካጽ ቬርድ የተባሉ የፖርቶጌስ ግዛት አሉ።

እነዚህ ያመለከትናቸው ደሴቶች ካንዳንድ በቀር ፍሬያም መሬትና መልካም አየር ያለባቸው ናቸው።

እንግዲህ ወደዚያ ላገራችን የሚቀርብ የዓለም ክፍል እንሻገር።

# እስያ።

የእስያ ስፋት የመላው ዓለም ሲሶ ያህላል። በስተ ሰሜኑ ለእስያ የአርቲኮ (ውርጭ) ውቅያኖስ፥ በምዕራቡ ኤውሮፓ፥ ጥቁር ባሕር፥ የማርማራ ባሕር መሀከለኛ ባሕርና የኤርትራ ባሕር፥ በደቡብ የህንድ ውቅያኖስ በምሥራቅ ደሞ ሰላማዊ ውቅያኖስ ከበውታል። በእስያ ሁሉ ዓይነት አየር ይገኛል ብርቱ ብርድ በሰሜን፥ ሃሩር በደቡብ። የእስያ ሕዝቦች ከ፰፻፳፭ ሚልዮን የሚበልጡ ናቸው። የሚበዙ ከካውካሲና ከሞንጎሊ ነገድ ናቸው። የበለጠ የሞንጎሊ ሃይማኖት ቡዲስሞ ነው። የካውካሲኣ ሃይማኖታቸው እስልምና ወይም ብራሚስም ወይ ደሞ ፓርሲስም ነው።

## የቱርክ እስያ።

ቱርክ አስቀድሞ ሰፊና የሰለጠነ መንግሥት ነበረ፥ ባለፈው ጦርነት ግን እየደከመና እያነሰ ሄደ። ግን ያነን ከሱ በታች ሲገዛ የነበረ፥ እንደነ ፓለስቲና ሶርያና ሞስጶታምያ፥ ገና ወራሹ ማን እንደሆነ እርግጡን ስላልታወቀ፥ የእገሌ ግዛት ነው ብለውን ልንጽፍ አይቻለንም። የእስያ ቱርኪ ህዝብ ፲፯ ሚልዮን የሚያህል ነው።

ትንሽ እስያ ከመሀከለኛ ባሕርና ከጥቁር ባሕር መሀከል ነው። ዋና ከተማው ስሚርና፥ ሕዝብዋ ፫፻፺ ሺሕ ነው። ያለችበት ስፍራ ከባሕር ዳር ነው።

አርሜንያና ኵርዴስታን ከትንሽ እስያ በስተ ምሥራቅ ናቸው። አገሩ ደጋ ነው። ያነን ከፍ ያለ የአራት ተራራ፥ የኖህ መርከብም ቆመች የሚባለውም በዚያ ነው። ከርሜንያ የሚገኝ ሐይቅ ዋን ይባላል፥ ውሀውም ጨው ነው። አርሜኔዎች ከብዙ ዘመን ጀምረው በቱርክ ተጨቍነው ይኖሩ ነበር፥ ቱርኮችም ከጭከናቸው የተነሳ ካገር እየገቡ ብዙ ሰው ይገድሉ ነበር። ዋና የአርሜን ከተማ ኤርሴሩም ትባላለች። ከጦርነት በኋላ ግን ከቱርክ እጅ ወጥተው የራሳቸው መንግሥት ሆኑ። እነዚያ ከርሜኒያ አጠገብ ያሉ ዮርጄአና አሴርበጃ ደሞ እንዲሁ ከቱርክ መከራቸውን ሲያዩ ነበሩ። አሁን የአርሜንያ ገዥ ተቀምጦባት ያለ ከተማ ኤሪባን ናት።

## ሶርያ ከፓለስቲና ጋራ።

ከሶርያ ገመገም እለዚያ የሊባኖስ ተራሮች የተባሉ ጠረፍ እናገኛለን። ያነን መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነብ ሁሉ የሚያውቀው የዮርዳኖስ ወንዝም ከዚያ ጨው የሆነ የሞት ባሕር ይፈሳል። ያች ደማስቆ የተባለች የንግድ ከተማና ቤሩት ከዚያ ናቸው ደማስቆ ፫፻፺ ሺሕ ሰዎች አሉባት። ከፓለስቲና (ከነአን) ደሞ ያች ከዓለም በሞላው የታወቀች የየሩሳሌም ከተማ በደጋው ከይሁዳ አገር አለች። ከመሀከልዋና ከያፋ የወደብ ከተማ ደሞ የብረት መንገድ ተበጅተዋል።

## መሰጶታምያ።

ጢግሮስና ኤፍራጥስ የሚፈስበት አገር ነው። በፊት ብዙ ሕዝብ የነበረውና ፍሬያም አገርም ኑሮ፥ አሁን ግን በሁሉ አንስዋል። ያገሩ ዋና ከተማ ባግዳድ ትባላለች ፪፫ ሺሕ ሰዎችም አሉባት። የባቢሎን ፍራሽ በኤፍራጥስ ዳር፥ የነነዌም በጢግሮስ ዳር ይገኛሉ።

## ዓረብ።

ዓረብ በስተ ምዕራብዋ ከኤርትራ ባሕር የምትጋጠም የደሴት እኵል ናት። መዲና ያለችበት ክፍል ግዛቱ ከቱርክ በታች ነው። ግን ኦማን የተባለ ታችኛው ክፍል ከገዛ ራሱ የሚገዛ ሱልጣን አለበት። ያገር ውስጥ እንደ በረሃ ኦማን ግን ፍሬያም። የዓረብ ሕዝቦች ፬ ሚልዮን ያህላሉ።

# የእንግሊዝ ግዛት ከሰሜን ምዕራብ። እስያ።

ቆጵሮስ አንዲት ከትንሽ እስያ ከትንሽ እስያ በታች ከመሀከለኛው ባሕር ያለች ደሴት ናት። ዋና ከተማዋ ኒኮሲአ ትባላለች።

ዓደን አንዲት ከዓረብ በስተ ደቡብ በዳር ያለች ከተማ ናት።

ፔሪም አንዲት አለት የሞላች፥ ፋሮ (ትልቅ ፋኑስ ያለበት ግምብ) ያለባት ደሴት ናት።

## ፋርስ።

ፋርስ ሰፊ አገር ነው። ግን ሲሶው በረሃ ነው። ከተራሮቹ መሀከል ከወንዞቹም አጠገብ ግን ብዙ ዓይነት ፍሬ የሚያፈራ ፍሬያም መሬት ይገኝበታል። ያ አገር በአልማዝ በዕንቍ በወርቅና በብር ሃብታም ነው። ባላገሮቹም በዚያ የሚሰሩት የሀገር ልብስና ስጋጃ ተመስግነዋል። ሕዝቡ ፱ ሚልዮንና ፫፻ ሺሕ የሚያህሉ ናቸው። በዚያ ያለች ተሄራን የተባለች ከተማ ፪፻፹ ሺሕ ነፍሳት አሉባት። በዚያ እንደ ንጉሥ ሁኖ አገር የሚገዛ ሻህ ነው።

## አፍጋኒስታን።

አፍጋኒስታን በሁሉ ወገኑ ወገኑ በመሬት የተከበበ ባሕርን የማይነካ አገር ነው። እሱም በምዕራብ ከፔርሲያ፥ በሰሜን ከባሉኺስታን በምሥራቅ ከህንድ ጋራ ይገናኛል። ሕዝቡ ፮ ሚልዮን የሚያህሉ ናቸው። እነርሳቸው ከእስያ ሰዎች ሁሉ የበለጠ ብርቶችና ትዕግስተኞች እንደሆኑ፥ ተወርቶላቸዋል። ስለዚህም አገራቸው በሌላ አልተገዛም። ያነን አገር የሚገዛ ኤሚር ይሉታል፥ ከካቡልም ይቀመጣል። አገሩ ተራራ የሞላ ነው። ህንዲኩሽ የተባለ ተራራ ከፍታው ፯ ሺሕ ሜትሪ ያህላል። ስለ አየሩ ደሞ ፋርስን ይመስላል። ከዚያ በደጋው ያሉ ተራሮች ብርቱ ብርድ፥ በለዚያ ከተራሮች መሀከል ያሉ ሜዶችም በበጋ ሃሩር ነው የሚሆነው።

## ባሉኪስታን።

ይህ አገር ያለ ከአፍጋኒስታንና ከዓረብ ባሕር መሀከል ነው። ሕዝቦቹ ከእንግሊዝ መንግሥት ስልጣን በታች ናቸው ቍጥራቸውም ፱፻ ሺሕ ያህላል። የሚበዙት ዘላኝ ናቸው። ያገሩ የሃይማኖት እስልምና ነው። በተቀረውም ባላገሮቹ መልካም ስርዓት ያልተማሩ ስድ መሄድ የሚወዱ ናቸው።

## ህንድ።

ህንዲ ብዙ ዓይነት ሃብትና ደስታ ያለበት አገር ነው። ስፋቱ ሶስት እጅ ኢትዮጵያን ያህላል። ያገሩ እኵሌታ በስተ ደቡብ ባሕርን ይነካል፥ በሰሜንም ከቺና ጋራ ይገናኛል። ሕዝቡ ደሞ እስከ ፫፻፲፭ ሚልዮን ይሆናል። ከኔፖልና ቦታን የተባሉ አገሮች በቀር የህንዲ አገሮች በሞላው ከእንግሊዝ በታች ነው። ከለዚ በያገሩ የሚዳኙ ጎቤርኔር የሚልዋቸው በላይ ደሞ የእንግሊዝ ንጉሥ እንደ ራሴ ተሹምዋል። ከህንድ ሰዎች ሶስት ሩብ የሚያህሉ ከኢንዱ ነገድ ናቸው። በዚያ አገር የብዙ ነገድ ሕዝብ ተቀምጥዋል፥ እንደ ጎንዲ ከሁሉ በፊት ያገር ዋኖች የነበሩ አሁን ግን ተገፍተው ከተራሮች ተቀምጠው ያሉ። ከነሳቸው በቀርም ዓረብ፥ ቱርኪ፥ አፍጋኒ፥ ፋርስ፥ የአይሁድና አርመን ከዚያ አገር ገብተዋል። በህንዲ ፻፵፯ ቋንቋ ሰው የሚነጋገሩባቸው አሉ። የህንድ ሕዝብ ከጥንት ጀምረው ካስት በሚሉዋቸው ክፍሎች የተከፍሉ ናቸው፤ ብራማኒ ከፍ ያለ ነገድ ወታደር፥ ነጋዴና አገልጋሊዎች። አሁን ግን እሱበሳቸው የማይቀራረቡ በመከራና በሞት ግዜ የማይረዳዱ ብዙ ሺሕ ካስት ሁነዋል። የሚበዙ ደሞ ለብዙ ሺሕ ጣኦት የሚሰግዱ አረማውያን ናቸው። ያገሩ ሃይማኖት ብራሚስም ነው የሚባል። የበለጡ አማልክታቸው፣ ብራማ፥ ዊሽኑና ሲባ ናቸው። የህንድ እስላም ፷ ሚልዮን ያህላሉ። እነዚያ በህንድ ያሉ የፋርስ ወገን ለፀሐይ እንደ አምላካቸው ምሳሌ ያደርጋሉ ለእሳትንም ይሰግዳሉ።

ከነዚያ እጅግ ከፍ ያሉ በስተ ሰሜን ያሉ ተራሮች ያነን እጅግ ከፍ ያለ ከፍታው ፲ ሺሕ ሜትር የሆነ ሂሚላይ ተራራን እናመለከታለን። ከሱ የሚመነጩ ወንዞች፥ ኢንዱስና ጋንጌስ ይባላሉ። ለጋንጌስ ቅዱስ ይሉታል። የበለጠ

በቤናረስ፥ ብዙ የከበሩና በብልኃት የተሸለሙ መቅደሶች የተሰሩባት ከተማ፥ ከጋንጌስ አጠገብ ያለች፥ በየዓመት ሚልዮኖች ያገር ልጆች ከኃጢአታቸው ሊነጹ ብለው ወደዚያ ሂደው ውሀ ይታጠባሉ።

በዚያ አገር በሞላውም በየወገናቸው የሚሰሩ አያሌ የወንጌል ማሕበር አሉ። በነሱ ወደ ክርስትና የተሳቡም ሚልዮናት የሚሆኑ ሰዎች ይገኛሉ።

የህንድ ዋና ከተማ ዴልሂ ትባላለች። ሌሎች ትልልቅ ከተሞችም ካልኩታ ፩ ሚልዮንና ፪፻፲፯ ሺሕ ሰው ያሉባት፥ ቦምበይ ከ፱፻፸ ሺሕ ሰዎችዋ፥ ፮፻ ሺሕ ሰዎች ያሉባት ማድራስም ናቸው።

በህንድም ሰይሎን የምትባል እንደ ገነትም የሆነች ፩ ሚልዮን ሕዝብም ያሉባት አንዲት ደሴት በስተ ደቡብ አለች። ዋና ከተማዋም ኮሎምቦ ትባላለች።

## ሲያም።

ሲያም ስፋቱ ኢትዮጵያን ያህላል። ህዝቡ ደሞ ፯ ሚልዮን ናቸው። በገዛጃቸው የሚገዙ የራሳቸው ንጉስ ያለቸው አርነት ያላቸው ሕዝብ ናቸው። እርሱ ዱር የሞላው በፍሬና እህል ሃብታም የሆነ አገር ነው። በደቡብ ከባሕር በምዕራብም ከህንድ ጋራ ይገናኛል። ዋና ከተማ ባንኮክ ትባላለች።

## የቺና ህንድ፡

ገዦቹ ፈረንሳ፥ ስፋቱ እንደ ኢትዮጵያ፥ ሕዝቡም ፲፯ ሚልዮንና ፫፻ ሺሕ ነው። በስተ ምዕራቡ ከቺና ሐይቅ ጋራ ይገናኛል። ዋና ከተማይቱም ሆኤ ትባላለች።

# የህንድ ምሥራቅ ደሴቶች።

ከእስያና ከአውስትራልያ መካከል ልክ የሌለባቸው ትንንሽና ቅልልቅ ደሴቶች አሉ። በነዚያ ደሴቶች የተቀመጡ ሕዝብም ፵ ሚልዮን ያህላሉ። እነዚያ ቍጥራቸው ብዙ የሆነ ለቺና በደቡብ ወገን የሚቀርቡበትም ፊሊፒኒ ይባላሉ የአሜሪካ ግዛትም ናቸው። ከሳቸው በታች ያሉም ሞሊኪ ይባላሉ። ሴሌበና ያባን ከሱ የሚበልጡ ናቸው። የሱማትራና የቦርኔዎ ስፋትም ኢትዮጵያን ያህላል። እኒህ ሕዝብ ክርስትና ሳይገባቸው የተዋረዱና ሰው የሚበሉ ነበሩ። በተቀረ ሁሉ ብዙ የታደሉ ደሴቶች ናቸው። የአራቸው ማለፍያ፥ መሬታቸውም ፍሬያም ነው የሚገዙም እኮሌቶቹ ከእንግሊዝ በታች፥ እኮሌቶችም ከኦላንድ በታች ናቸው።

## ቺና።

ቺና ከነዚያ ከሱ በታች የሚገዙ ቲቤት የምሥራቅ ቱርኬስታን ሞንጎሊአና ማንሹሪኣ ጋራ ስፋቱ ፲፪ እንደ ኢትዮጵያ። ሕዝቡም ፬፻፴ ሚልዮን ነው። እንግዲህ የቺና ሕዝብ ከሞላው ዓለም ሕዝብ ፩ ሩብ ናቸው። በምሥራቅ ከውቅያኖስ ሰላማዊ፥ በድቡብ ከህንድ፥ በሰሜን ከስርቤርያ ጋራ ይጋጠማል።

ቺና ከጥንት ጀምሮ ብልኃትና እውቀት የነበረው አገር ነው። የቺና ሰዎች ስራ የሚወዱ ትዕግስተኞችና ቻዮች ናቸው። ዋና ስራቸው ማረስ ነው። ከሰሜን ስንዴ፥ ባቄላ የባሕር ማሽላ፥ በደቡብም ሩዝ ይዘራል፥ የሱካር አገዳና ሻሂ

ደሞ ይተከላል። የቺና ሰዎች መብል ሩዝ፥ መጠጣቸውም ሻሂ ነው። ከሰው ብዛት የተነሳና፥ ያ ፍሬያም መሬት ሳይታረስ እንዳይቀር ብለው ሳስተው መርከቦችን የሚመስሉ ቤቶች እየሰሩ አእላፋት ሰዎች ከወንዝ ይሰፍራሉ። የቺና ሰዎች የሃር ልብስ በመስራት በሞላው ዓለም የተመሰገኑ ናቸው። አገሩ የሚገዛም አንድ ሕዝቦቹን የመረጡት የወንድማማች ሹም ነው። ስለ ሃይማኖታቸው ኮንፉሲኡስና ቡዳን ይከተላሉ። በየከተማው የሚኖሩ ሕዝቦች ብዙ ናቸው። ያች ከደቡብ በስተ ዳር የተሰራች ፔኪንግ የተባለች ዋና ከተማ ፩ ሚልዮን ሰው ሲንጋንና ሲኦንግታንግም አንዳንድ ሚልዮናቸውን ይዘዋል። ወደ ደቡብ አድርገው የሚፈሱ እሰከ አገር ውስጥም መርከቦች ሊያስገቡ የሚችሉ ትልልቅ የበለጡ ወንዞችም ሆአንግሆ ያንግ ጼ ኪአንግ ይባላሉ።

ቲቤት ከዓለም ሁሉ አገሮች ከፍ ያለ ደጋ ነው። ብርድ ስለ በረታበትም ሕዝቡ ፮ ሚልዮንና ተኵል ብቻ ያህላሉ። ዋና ከተማዪቱ ላሳ ትባላለች እርስዋም የዚያ ላማ የሚሉት ሊቀ ካህናትና የብዙ ሽሆች ካህናት ቡዲስትም መኖርያ ናት። እውቀታቸው ጥቂት ከጸሎቱ መዘወር ማዞርና ጥቂት ድጋም በቀር ለሕዝብ የማይጠቅሙ ሳሉ የሐቡ እኵሌታ ካህናት ይባላሉ።

የቺና ቱርኪስታን በስተ ምዕራብ የሚገኝ ፩ ሚልዮንና ፪፻ ሺሕ ሕዝብ ያለበት አገር ነው። የሕዝቡ እኵሌታ ካንድ ወዳንድ የሚጓዝ ስፍራን የሚለዋውጥ ዘላኝ ነው። መሬታቸው እጅግ ፍሬያማ አይዶለም። ዋና ከተማቸው ካሽጋር ትባላለች።

ሞንጎሊያ እልፍ እልፍ ብሎ በረሃ የሚመስል ደረቅ አገር ነው። ሕዝቦቹ ፪ ሚልዮን ያህላሉ፥ የሚበልጡቱም ስፍራ የሚለዋውጡ ዘላኞች ናቸው።

ማንሹሪኣ ከቺና በስተ ሰሜን ያለች ፳ ሚልዮን ሕዝብም ያሉባት አገር ናት። በማንሹሪኣ አገር ፍሬያሞች ሜዶች አሉ። በዳር ግን ተራራ የሞላው አገር ነው። ማለፍያ ዛፎች ያሉባቸው ሰፊ ዱሮችም በዚያ አሉ። ከዚያም ወርቅ፥ ብር፥ ብረትና የደንግያ ከሰልም ይገኛል። ዋና ከተማይቱ ሙከደን ትባላለች።

## ኮሬአ።

ኮሬአ ከማንሹሪኣ ጋር የተጣበቀ እኵሌታ ደሴት ነው። ሕዝቡ እስከ ፲፫ ሚልዮን ይሆናል። ያች ሴኦል የተባለች ዋና ከተማ ፩፻ ሺሕ ሰዎች አሉባት። አገሩ ሃብታም ሕዝቡም ባለ አእምሮና ንቁ ሕዝብ ነው። ከሕዝቡ የሚበዙቱ ቡዲስት ናቸው እንደ ቺና ሰዎችም የሞቱ አባቶቻቸውን ያመልካሉ። ወደ ክርስትና የሚሳቡና ስለ ሃይማኖታቸው ደስ ብሉዋቸው ውርደትና መከራንም የሚቀበሉ ብዞች ናቸው። የኮሬአ አገር የሚገዛ ከያፓን መንግሥት በታች ነው።

## ያፓን።

የያፓን መንግሥት የምንለው ከኮሬአ አጠገብ ያለ፥ ፮ ትልልቅ ደሴት ነው። የደሴቶቹ ስም እንዲህ ነው፥ ሆንዶ ዮጶ፥ ኪኡሲኡ፥ ካሳሊን ሲኮኩና ፎርሞሳም ከቺና ገምገም አጠገብ ያለች። ከሱ ጋራ የሚቈጠሩም ቍጥር የሌለባቸው ትንንሽ ደሴቶች በዚያ ይገኛሉ። የፓን ሕዝብ ለም ነው። አገሩ ትንሽ ሳለ ፶ ሚልዮን ሰዎች ሰፍረውበታል። ከተሞቻቸውም ብዙ ሰው የሰፈረባቸው ናቸው። ቶክዮ የምትባል የያፓን ዋና ከተማ ፪ ሚልዮንና ፪፻ ሺሕ ሰው ኦሳካ ፩ ሚልዮንና ፪፻፳፫ ሺሕ ኪኦቶ ፬፻፶ ሺሕ መሬት ይይዛሉ። መሬታቸው ብዙ ዓይነት ፍሬ የሚያፈራ መሬት ነው። የያፓን ሕዝብ ለስራ ፈጣኖች ናችወ። የፈረንጆች ስርዓት ሊማሩ ብለውም ብዞች የያፓን ጐበዛዝት ወደ ኤውሮፓና አሜሪካ ቤት ትምህርት ይገባሉ። ባገሩ መሀከልም በወንጌል ማሕበር የተሰሩ ብዙ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ።

መንግሥትም ብልኀት የሚያውቁ ሰዎች ከባዕድ አገር እየጠራ ወዳገሩ አገባ። በጥቂት ዓመታትም ሕዝብ በሞላው በብልህነት በጮሌነት ከፍ አለ። ከትልቁ መስኮብ መንግሥት ጦርነት የገጠሙ ግዜ፥ ሻሩት። ያገራቸው አገዛዝም ታድሰዋል። አስቀድሞ ሥልጣን ሁሉ ከቄሳር እጅ ነበረ፥ አሁን ግን እንደ ኤውሮፖች መንግሥት አገዛዝ አጤው፥ ከለዚያ ሕዝብ የመረጣቸው ሹማምት ሁኖ አገርን ይገዛል። በገዛ አገራቸው የተሰሩ የጦር መርከቦችና ከዓለም ባሕሮች የሚመላለሱ የንግድ ባቡሮች አሉዋቸው። በዚህ በኋለኛው ጦርነትም ስማቸው ታውቅዋል።

## ሲቤርያ።

ስፋቱ ፳፬ ኢትዮጵያን ያህላል። ሕዝቡ ግን ፰ ሚልዮን ብቻ ነው። በሰሜን እስከ ውርጭ ውቅያኖስ ወይ ውቅያኖስ አርቲክ፥ በደቡብምም ቺናን ይነካል። የበለጠ በበጋ ሊፈር ብርድ ይበረታል። መከሩ (ሌቴ) ግን ሙቀት ይበረታበትና አጭር ይሆናል። በስተ ደቡብ ስንዴና ገብስ ይዘራል። በዚያም የብረት ዓይነት ይገኛል። የሩስያ ወይ መስኮብ ቄሳሮችም የበለጠ ለዓመጸኞችና ለመንግሥት ምቀኞች ለቅጣታቸ ብለው ወደዚያ ይሰዱዋችዋል። የሲቤርያ ዋና ከተማ ቶቦልስክ ትባላለች።

ቱርኬስታን።

ቱርኬስታን ከሲቤርያ ጀምሮ እስከ ፔርሲአ የሚደርስ አገር ነው። ሕዝቡ እስከ ዘጠኝ ሚልዮን ያህላል። ከወንዞቹ ዳር ፍሬያም መሬት አለ፥ በተቀረ ግን መሬቱ አሸዋ መሳይ ነው። ባላገሮቹ ከብት ያረባሉ።

ባገሩ ውስጥም ውሀቸው ጨው የሆነ ሁለት ትልልቅ ኡራልና በልከሽ የተባሉ ሐይቆች አሉ። በዚያም በበጋ ብርድ፥ በመከር ደሞ ሃሩር ይሰለጥናል። ዋና ከተማው ታሽከንድ የተባለች ፩፻፶፮ ሺሕ ሰው ያሉባት ናት።

## ካውካሲአ።

ካውካሲአ በሰሜን ወገን ከመስኮብ ጋራ ይገናኛል። ሕዝቡ ወደ ፲ ሚልዮን አድርጎ ነው። ያች ቲፍሊስ የተባለች ዋና ከተማዩቱም ፩፻ ሺሕ ሰዎች አሉባት። አንዳንድ ክፍል ካገሩም ተራራ የሞላው ነው፥ በተቀረም ፍሬያም መሬት ይገኝበታል ከባኩ የተባለ ስፍራ ደሞ ጋዝ ይወጣል።

# ኤውሮፓ።

ኤውሮፓ ከእስያ በስተ ምዕራብ፥ ከመሀከለኛ ባሕርም በሰሜን ያለ ዓለም ክፍል ነው። ስፋቱ ከሶስቱ ዓለም ክፍል ያነስ፥ ከአውስትራልያ ግን የበለጠ ነው። እንዲሁ ሳለም ከሌሎቹ ይልቅ ሃብታምና የሰለጠነ የዓለም ክፍል ነው። ምክንያቱም የሚከተለው ነው። የኤውሮፓ አየር ለብ ያለ ስለ ሆነ። ሁለተኛ የከበረ የደንግያ ረገድ (ሜኔራል) እንደ ብረት፥ መዳብ፥ ደንግያ ከሰል እንዲሁ ያለ ነገርም ስለ ሞላው። ሶስተኛ፤ ባሕሩ ቅርብ ላገሩ ሁሉ የሚገባበት ስለ ሆነ፥ ለንግድ የተመቸ ነው። አራተኛ፤ ባላገሮች ሃብት የሚሰጥም የነን ፍሬያም መሬቱንና የዝናሙ ብዛት ነው። ኤውሮፓ እንደዚህ መሆኑም፥ የኤውሮፓ ሰዎች ለስራ ስለማያፍሩ፥ ከሌሎች ሕዝብ የበለጠ ስለ ነቁ፥ የፈጠኑና ትዕግሥተኞች ሕዝብ ስለ ሆኑ ነው። ከዚህ ሁሉ በላይም፤ ያነን ከሌላ ይልቅ ለሰው ልቦና የሚሰጥና የሚያነቃ ክርስትና ከጥንት ጀምሮ በመሀከላቸው ስለ ስለጠነ ነው።

አገሩ ትንሽ ሳለ፥ ሕዝቡ ግን ብዙ የሆነ የቤልጊክ አገር ነው። አገሩ ሰፊ ሳለ፥ ሕዝቡ ግን አነስ ያለ ደሞ ኖርዌ የተባለ መንግሥት አለ።

እለዚያ ፬፻ ሚልዮን የሚሆኑ የኤውሮፓ ሰዎች ከካውካሲኣ የተባለ ነገድ ናቸው። ይህ ነገድም ባ፬ ይከፈላል ፩ ከልቲ በምዕራብ ወገን ፪ ጀርማኒ ወይም ተብቶኒኪ በመሀከልና በሰሜን ወገን፥ ፫ ሮማኒ ወይም ግሪክ ላቲን በደቡብ ፬፤ ስላቦኒ በምሥራቅ።

መሰረታቸው ከነገደ ከልት የሆኑ አሁን በእንግሊዝና ስሜን ምዕራብ ፈረንሳም ይቀመጣሉ። ለነዚያ የከልት ነገድ ጀርማኒ መጥተው እንዳያስለቁዋቸው አስቀድመው ከዳንማርክ አንስቶ እስከ እስፓኛ ያለ አገር ሰፍረውበት ያእል ከእንግሊዝ አገር ደቡብ ወገን ነምሳ በሞላው አውስትርያ፥ ስካንዲናቢኣ፥ ሆላንዲኣና በልጊኣ ነው። ከነገደ ግሪክ ላቲን የሚቈጠሩ ፈረንሳዎች፥ ስፓኛ፥ ፖርቶጌስ፥ ኢታልያ ሩሜንያና ግሪክ ናቸው። የመስኮብ ሰዎች ፖሎንያ ሴርቢኣ ቡልጋሪኣና ቦሄሚኣ ከስላቦኒ ነገድ ናቸው። የሞንጎሊ ነገድም እንደ ላፖንና የፊላድ ሰዎች በሰሜን ማጉኣሪ በኡንጋሪኣ ከልሙክና ታርታር ከመስኮብ አገር በስተ ደቡብ በቱርክም ደሞ አሉ። ፯ ሚልዮን የሚያህሉ አይሁዶችም ወደ ኤውሮፓ በሞላው ተዘርተው፥ የበለጠ ግን ከፖሎንያ ይገኛሉ።

ከለዚያ የኤውሮፓ ክርስትያኖች ፩፻፹፫ ሚልዮን ካቶሊክ ፩፻፲ ሚልዮን ፕሮቴስታንት ፩፻፲ ሚልዮን ካቶሊክ ግሪክ ናቸው። እለዚያ የቶብቶኒክ ነገድ ሃይማኖት ፕሮቴስታንት የላቲን ነገድ ሃይማኖት ካቶሊክ ሮማ እለዚያ የስላቦኒ ነገድ ደሞ የግሪክ ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ይታመናሉ።

ኤውሮፓ መንፈሳዊና ዓለማዊ ትምህርት ጥበብም የሰለጠነበት ዓለም ክፍል ነው። በመንደሮች ልጆች የሚማሩበት ትምህርት ቤት፥ ከከተሞችም ከፍ ያሉ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ። ከሚበዙ አገሮችም ልጆች በውድም ቢሆን በግድ ልጆች ንባብ ሊማሩ የተደነገገ ነው። ትምህርት የበለጠ በጀርማኒና በከልት ነገድ ነው የሰለጠነ። ከሳቸው በኋላም የላቲን አገሮች ናቸው። ከነገድ ስላቦኒ ግን ማንበብ የሚችሉ ጥቂቶች ናቸው።

በነምሳ አገር ከ፩፻ ሽሕ ሰዎች ፩፻፴፱ ብቻ ናቸው ማንበብ የማይችሉ። በሱዌድም ከ፩፻ ሽሕ ሰዎች ፴፪ ያልተማሩ ይገኛሉ። በእንግሊዝ አገር ከ፻ ሰዎች ፰ ናቸው መጽሐፍ የማያነቡ። ያልተማሩ የበለጠ በኢርላንዳ ናቸው የሚገኙ። ያልተማሩ በፍራንስ ፴፫ በኡንጋሪኣ ፶፩ በኢታልያ ፰፬ በመስኮብ ፹፰ ከመቶ ናቸው።

ለዘመቻ ቀሊል ነገር የሚያደርጉና ወደ ፈቀድኸው በተሎ ለመድረስ የሚያስችሉም እለዚያ ልክ የሌላቸው በኤውሮፓ ያሉ የብረት መንገድ ናቸው። ከስእላቸው ብታይም መርበብ ይመስላሉ።

በሚከተሉቱ ክፍሎች ስለ ኤውሮፓ በያገሩ አሳጥረን እናመለክታለን።

## መስኮብ።

ከኤውሮፓ በምሥራቅ ወገን የሚገኝ አገር ከዚህ ብርቱ ጦርነት በፊት የኤውሮፓ በሞላውን እኵሌታ ያህል ነበረ። ሕዝቡም ፸፬ ሚልዮን ነው የነበረ። እሁን ግን ከዚያ በጭከና የሚጨቍናቸው የመስኮብ ግዛት አንዳንድ አገር አርነት ወጥተዋል። እንደነ ፊንላንድ ፐሎንያና ኡክራይና የተባሉ አሁን ግን ከዚያ በጭከና የሚጨቍናቸው የመስኮብ ግዛት፤ አንዳንድ አገር አርነት ወጥተዋል። እንደነ ፊንላድ ፐሎንያና ኡክራይና የተባሉ፥ አሁን ባገራቸው ሹም የሚገዙ ያሉ አገር። የመስኮብ አገር በዚያ ጻር የሚሉት እንደ ፈቀደ የሚያደርግ ገዢ ይገዛ ነበረ በጦርነት ግዜ ደም ቦልሴቢክ የሚልዋቸው አንድ የሴራ ወገን ተነሥተው ጻርን ገድለው የራሳቸው አገር ዋኖች አደረጉ፤ ለግዛታቸውም ብዙ ደም ማፍሰስ ተከትለው።

ያች ፔትሮግራድ የምትባል የመስኮብ መናገሻ ከተማም ከፊንላድ ባሕር ጎልፍ ናት ተሰርታ ያለች። በፊት ሕዝብዋ ፩ ሚልዮንና ፰፻፸ ሽሕ ነበረ። እርስዋ በትልቅነትዋ ሆነ በማማርዋ የምታስደንቅ ከተማ ናት። ካገር ውስጥ ያለች

ሞስከዋ የተባለች ከተማም ትልቅ ናት። ፩ ሚልዮን ሰውም አለባት። የፖሎንያ ህዝብ ፴፬ ሚልዮን ናቸው። ዋና ከተማዪቱ ዋርሽኡ ትባላለች። ፊንላዳ አገሩ ሰፊ ሳለ ሰዉ ፫ ሚልዮን ብቻ ነው። ያች በቦችንያ በሕር ኀልፍ የተሰራች የፊላንዳ ዋና ከተማ ደሞ ሄልሲንግፎርስ ትባላለች። የኡክራይና ሕዝብ ፴፭ ሚልዮን ናቸው።

## የጀርመን አገር።

አስቀድሞ ይህ ከመስኮብ ወደ ምዕራብ የሚገኘ የጀርመን አገር አንድ ቄሳር የሚገዛው የሰለጠነ መንግሥት ነበረ። ቄሳሩ ከተለወጠ በኋላ ግን፥ በመንግሥቱ የሚገዙ ከሕዝብ የተመረጡ ሹማምንት ናቸው። የመንግሥት ከተማ በርሊን ትባላለች። እርስዋ ግሩም ሁና ያማረች ፪ ሚልዮንና ፰ ሺሕ ሰዎች ያሉባት ከተማ ናት። ሁለተኛይቱም ያች ማለፍያ አደራሾች ያሉባት፥ የበለጠች የምትባል፥ ፩ ሚልዮን ሰዎች ያሉባት የኤልባ ወንዝ የተሰራች ሃምቡርግ የተባለች ከተማ ናት።

የጀርመን ሕዝብ በሞላው ፷፪ ሚልዮን የሚያህል ነው። ከብዙ ዘመን ጀምሮ ኢንዱስትርያ በዚያ ስለ በዛም፥ ብዙ ዓይነት እቃ ከነምሳ ወደ ሁሉ ዓለም ይሄዳል።

## አውስትሪኣና ኡንጋሪኣ።

እነዚ፥ ከጀርመን ወደ ደቡብ ምሥራቅ ያሉ ሁለት አገሮችና፥ ቦሄምያ፥ ቦሲኒኣ፥ ሄርጼጎቢናንም እስከ ቅርብ ግዜ አብረው ከአንድ ቄሳር በታች ይገዙ ነበሩ። አሁን ግን ተለያይተው በያገራቸው እያንዳንዱ በወንድማማች ሹም ይገዛል። የዚያን አገር ልጆች ብዙ ልዩነት ያለባቸውና ከብዙ ነገድም ናቸው። የአውስትሪኣ ሕዝብ ፴፪ ሚልዮን ነው።

የአውስትሪኣ መናገሻ ከተማ ቤን የኡንጋሪያ ቡዳፔስ፥ የቦሄምያ ፕራግ።

## የእንግሊ አገር።

የእንግሊዝ አገር ከኤውሮፓ አገሮች በባሕር የተለየ በሰሜን ምዕራብ ወገን ከጀርመንና ፍራንስ አገር አንጻር ነው። መንግሥቱ ከ፫ ይከፈላል፤ ኢንግላንድ፥ ስኮትላንድ፥ ኢርላንድ። እርሱ ከሌሎቹ በዓለም ያሉ አገሮች የሰለጠነ አገር ነው። የሕዝቡ ቍጥር ፵፯ ሚልዮን ነው። ንጉሥ አለባቸው ግን ንጉሥን ለማንገሥ የበለጠ ሥልጣን ከፓርላሜንቶ የተባለ ሸንጎ እጅ ነው። እርሱም ከሁለት ክፍል ይከፈላል፤ ከላይኛው ክፍል ያባት ልጆች ይሾሙና ይወርሳሉ፥ ከታችኛው ክፍል የሚገቡ ግን በሕዝብ ተመርጠው ይሾማሉ። የመንግሥት ከተማ በተምሰን የተባለ ወንዝ ተሰርታለች፥ እንደስዋ የሰፋና ሕዝብዋ የበዛ ከተማም የለም። እርስዋ ፯ ሚልዮንና ፭፻ ሺሕ ሰዎች ያሉባት ሎንዶንም የተባለች ናት።

በእንግሊዝ አገር ብዙ ዓይነት ኢንዱስትሪያ ሞተዋል። የእንግሊዝ ንግድ መርከቦችም በሞላው ዓለም ባሕር ይታያሉ።

## ፈረንሳ።

ከእንግሊዝ አገር የፈረንሳ አገር ይሰፋል። እርሱም ከጀርመንና አውስሪኣ በስተ ምዕራብ ይገኛል። ሕዝቦቹ ሁሉ ፵ ሚልዮን ናቸው። ያ አገር በወንድማማች ሹም ነው የሚገዛ፥ ገዡም ፕሬሲዳን ናቸው የሚሉት። እርሱም ያገሩ ገዧ

ሊሆን በየ፯ ዓመት ከሕዝቡ ይመረጣል። ዓመቱ ከጨረሰ በኋላ፥ ሕዝቡ እንደገና ባይመርጠው ሹመቱ ለተመረጠው አዲስ ሹም ይሰጣል።

ያች ከሰን ወንዝ የተሰራች የፈረንሳ መናገሻ ከተማ ፓሪ ትባላለች፡ ሕዝብዋም ፪ ሚልዮንና ፰፻፶ ሺሕ ናቸው። ስለ ማማርዋና ጌጥዋ በዓለም ሁሉ የተመሰገነች ናት። ስለዚህም እርስዋን ለማየት አእላፋት እንግዶች በየዓመት ወስደዋ ይደርሳሉ። ያች ኮርሲካ የተባለች ደሴትም ከፈረንሳ ነው ቍርጥዋ።

## እስፓኛ።

የእስፓኛ አገር ስፋቱ የፈረንሳ አገርን ያህላል፥ በስተ ሰሜንም ከሱ ጋራ ይገናኛል። ህዝቡ ሁሉም ፳ ሚልዮንና እኩል ነው። ያች ባገሩ መካከል ተሰርታ ያለች መናገሻ ከተማም ማድሪያ ትባላለች። ህዝብዋ እስከ ፭፻፫ ሺሕ ድረስ ይሆናሉ። ያገሩ መንግሥት ካባት ወደ ልጅ የሚያልፍ ነው፥ ግን ንጉሡ ምንም ያባት ልጅ ቢሆን ከሕዝቡ ፈቃድ ወጥቶ የሚያደርገው ነገር የለበትም።

## ኢታልያ።

የኢታልያ አገር እንደ ፈረንሳና ስፓኛ ሰፊ አይዶለም፥ ግን ሕዝቡ ከሳቸው የበለጠ ለም ነው። ያነን በደቡብ በመህከለኛ ባሕር በምሥራቅ በአድርያቲኮ ባሕር በምዕራብ በትሬኖ ባሕር የተከበበ እኩሌታ ደሴት የሆነ፥ የኢታልያ መሬት ብዙ ዓይነት ፍሬ የሚያፈራ ፍሬያም መሬት ነው። አየሩ መልካም፥ ማየቱ ደስ የሚያሰኝ ከጥንት ጀምሮ ብዙ የሚያስጐመጅ ነገር ያለበት ስለ ሆነም ለማየት ብቻ ከሩቅ አገር እንግዶች ይመጡበታል። መናገሻ ከተማዪቱ ያች ፭፻፸፭ ሺሕ ሰዎች የሚገኙባት ሮማ ናት። ያች ከኢታልያ ደቡብ በዳር ያለች ባጠገብዋም ያነን እሳተ ገሞራ ያለባት ተራራ ያለባት ናፖሊ የምትባል ከተማ ከሮማ ትበልጣለች።

የኢታልያ ሕዝብ በሞላው ፴፰ ሚልዮን። የኢታልያ ንጉሥ በሕዝቡ ፈቃድ በተወሰነ ስልጣንና ሕግ ይነግሳልና ይገዛል። እነዚያ ስቺልያና ሳርደኛ የተባሉ ደሴቶችም ከኢታልያ አገር ነው ቍጥራቸው።

## የግሪ አገር።

የግሪክ አገር ከኢታልያ በስተ ደቡብ ምሥራቅ ያለ ትንሽ አገር ከደሴታቱ ጋራ ነው። ስፋቱ የኢትዮጵያን ስምንተኛ እጅ ያህላል። ያች ከሳቸው በታች ያለች ክሬታ የተባች ትልቅ ደሴት ግን የራስዋ መንግሥት ናት። ግሪካውያን ፫ ሚልዮንና ፯፻ ሺሕ ይሆናሉ። ያገሩ መናገሻ ከተማ አቴን ፩፻፫ ሺሕ ሰው አለባት። ያ አገር ተራሮች የሞላውና መልካም አየር ያለበት ነው። የመንግሥቶቹ አገዛዝ እንደ ኢታልያን ነው።

## ቱርክ ኤውሮፓ።

የቱርክ አገር በኤውሮፓ ከመህከለኛ ባሕር ጀምሮ እስከ ጥቁር ባሕር ይደርሳል። ሕዝቡ ፮ ሚልዮን ነው። ያች ኮስታንቲኖፖሊ የተባለች መናገሻ ከተማዪቱ በመህከለኛ ባሕርና ጥቁር ባሕር የሚያጋጥም አንገት ናት ተሰርታ ያለች።

እርስዋ ማየትዋ ያማረ፥ ፩ ሚልዮንና ፪፻ ሺሕ ሰውም ያለባት ከተማ ናት። ያገሩ መሬት ፍሬያም ነው። ከግርግር በኋላም የሱልጣኑ ስልጣን በኤውሮፓ ስርዓት ተወስንዋል።

አልባንያ የተባለ ፰፻፶ ሺሕ ሰው ያሉበት መንግሥትም ከቱርክ እጅ አርነት ወጥተዋል።

## ቡልጋሪአ።

ቡልጋሪአ ከቱርክ በስተ ስሜን ነው። ሕዝቡም ፬ ሚልዮንና ፫፻ ሺሕ ያህላሉ። የጻሩን አገዛዝ በሕግ የተደነገገ ነው። መናገሻዪቱ ከተማ ሶፊአ ትባላለች።

## ሩመኒአ።

ሩመኒአ ከቡልጋሪያ በስተ ሰሜን ያለ ትንሽ መንግሥት ነው። ሕዝቡ ፲፫ ሚልዮን ይሆናሉ። ያች ቡካሬስት የምትባል ያገሩ መናገሻ ከተማ ሕዝብዋ ፫፻ ሺሕ ናቸው።

## ሴርቢአ።

ይህ ትንሽ ሴርቢአ የተባለ በምሥራቅ ወገን ከቡልጋሪአና ሩማኒአ ትገናኛለች፥ ሕዝቡ ፬ ሚልዮን ነው። መናገሻ ከተማዪቱም በልግራድ ናት። ከባሕር ዳር ባጠገቡም ያነን በጣም ትንሽ የሆነ የሞንቴኔግሮ መንግሥት ይገኛል።

## ፖርቶጋል።

ይህነን አገር በስተ ምሥራቅ ከስፓኛ፥ በምዕራብ ደሞ ውቅያኖስ አትላንቲክን ይነካል። ሕዝቡ ፭ ሚልዮንና ፭፻ ሺሕ ነው። ገዡ የወንድማማች ሹም ነው። ያገሩ መናእሻ ከተማ ሊስቦና ትባላለች፥ ሕዝብዋም ፫፻፷ ሺሕ ነው። መሬቱ ፍርያም ነው፥ የበለጠ ደም ብዙ ወይን ይገኝበታል።

## ሱዊስ።

ሱዊስ ከኢታልያና ከነምሳ መሀከል የሚገኝ ተራሮች የሞሉት፤ ከፍ ያለ አገር ነው። እነዚያ በሱ ያሉ አልፒ ተራሮች፥ እኩሌታቸው እስከ ፭ ሺሕ ሜትር ከፍ ያሉ ናቸው። በዚያ የሚገዛ የወንድማማች ሹም ነው። ሕዝቡ ፫ ሚልዮንና ፫፭ ሺሕ ናቸው። ያች ሱሪክ የተባለች ያገሩ መናገሻ ከተማም ፩፻፺ ሺሕ ነፍሳት አሉባት።

## ቤልጊክ።

በልጊክ ከፈረንሳ በላይ፥ በእግሊዝ አገር ፊት ለፊት ነው ያለ። አገሩ ትንሽ ሳለ፥ ፯ ሚልዮንና ፮፻ ሺሕ ሰው አለበት። ያች ብሩሴል የተባለች ያገሩ መናገሻ ከተማ ፫፻ ሺሕ ነፍሳት አሉባት። የንጉሡ ስልጣን እንደነ ኢታልያ ነው።

### ሆላንድ።

ሆላንድ ከበልጊክ በላይ ያለ ትንሽ ፭ ሚልዮን ተእኩል ሰዎች ያሉበት መንግሥት ነው። ያች አያ የተባለች መናገሻ ከተማዪቱ ፫፻፲ ሺሕ ሰው አለባት። የመንግሥቱ አገዛዝ እንደ ጐረቤቶቹ ነው።

### ዳንማርክ።

ዳንማርክ ከነምሳ አገር የገጠመ እኩሌታ ደሴት ነው፥ ከሱ ጋራ የሚቈጠሩም አያሌ ደሴቶች በዙርያው አለበት። ከደሴቶቹም ኢስላንዳ የተባለ የውርጭ አገርን እናመለከታለን። እርሱ የሚገኝ በውቅያኖስ አትላንቲክ ነው። ከለዚያ በሰሜን ያሉ አገሮችም የራቀ ነው። በዚያ ማረስ የለም፥ ያገሩ ሰዎችም ኑሮዋቸው ከብት በማርባትና ዓሳ በማጽመድ ነው። በዚያን አገር አያሌ ሜትር ወደ ላይ የሚወረወር ፍሉ ውሀ ይገኛል። ያች ፭፻ ሺሕ ሰው ያለባት የዳንማርክ መናገሻ ከተማ ክኮፔንሃግ ትባላለች። የዳንማርክ በሞላው ሕዝቡ ፫ ሚልዮን ተእኩል ነው። የመንግሥቱ አገዛዝም በፊት እንዳልናቸው መንግሥታት ነው።

### ስዌድ።

ለሱዌድ የባልቲክ ባሕርና የቦቱንያ ባሕር ለይቶ ነው እንጅ፥ ከመስኮብ አገር ጋራ የገጠመ ነው። አገሩ ሰፊ ሳለ፥ ሕዝቡ ፭ ሚልዮን ብቻ ናቸው። እርሱ ወንዞችና ሐይቆች የሞሉት አገር ነው። ያች ስቶክሆልም የተባለች ባንድ ወገንዋ ካያሌ ደሴቶች የተሰራች ሕዝብዋ ፬፻ ሺሕ ናቸው። ስለ እነዚያ ሰፊዎች ዱሮች ዕንጨት ከሱዌድ ወደ ሁሉ ዓለም ይሄዳል። በዚያ አገር ብረትም ሞልቶ ይገኛል።

ያገሩ ንጉሥ በተወሰነ ሥልጣን ከሁለት በህዝብ የተመረጡት ማሕበር ጋራ ከሹማምንቱ ሁኖ አገርን ይገዛል።

### ኖርዌጅ።

ኖርዌጅና ሱዌድ ካንድ እኩሌታ ደሴት የተጋጠሙ አገሮች ናቸው። ፊተኛው በስተ ምዕራብ ውቅያኖስ አትላንቲክን፥ በምሥራቅ ደሞ ሱዌድን ይነካል። እርሱ ተራሮች የሞሉትና በብዙ ስፍራም ባሕር የሚገባው አገር ነው። ሕዝቡ ፪ ሚልዮን ተሩብ ብቻ ናቸው። የኖርዌጅ መናገሻ ከተማ ያች በደቡብ ያለች ክርስቲያን የተባለች ፪፻፵፫ ሺሕ ሰውም ያለባት ናት።

ስፔትሰብርግን የተባለች እጅግ ወደ ሰሜን ሳብ ያለች በውርጭ ውቅያኖስ መሀከል ያለች ደሴትም ከኖርዌጅ ጋራ ትቈጠራለ። ያች ደሴት የበለጠ የክሰል ደንግያ የሞላት ናት። ግን ከብርድዋና ከጨለማዋ ብርታት የተነሳ ባመት ጥቂት ወራት ብነው ሰው ሆነ እንስሳ ሊቀመጣት የሚችል።

## አሜሪካ።

አሜሪካ በስፋቱ ከዓለም ክፍሎች ሁለተኛ ነው። ከሌሎች ዓለም ክፍል በኋላ ስለ ተገኘ ደሞ አዲስ ዓለም ይሉታል። ለዚያ አገር በፊት የገባበትም ኮሎምቦ የተባለ የኢታልያ ልጅ ነው። በዓለም ሳይታወቅ ኑሮም፥ እርሱ በ፲፬፻፺፪ ዓመት ከክርስቶስ በኋላ ገለጠው። እርሱ በመጀመርያ አዲስ ዓለም ያገኘ አልመሰለውም ግን ህንድ መስሎት ነበረ።

ስለዚህም ባላገሮቹን ኢንድያን ብሎ ጠራቸው። በዚያ አገር የቈዩ ሕዝብ ሁለት ዓይነት ብቻ ነበሩ፤ ኤስኪሜስ በሰሜን ኢንዲያኒ በደቡብ። ያነን አዲስ ዓለም የያብት ዓይነት ሁሉ የሞላው፥ እጅግ ፍሬያም መሬትም ያለበት ዓለም ነው። በዓለም ከታወቁ በኋላ የበለጠ ከፈረንጆች አገር ብዙ ሕዝብ ወደዚያ አገር ገቡና በጥቂት ጥቂት አገሩን ወረሱት። ብዙ ኔግሮም በዚያን አገር ሰፍረዋል። የበለጠ በሰሜን አሜሪካ ለንግግር የሚሆን ቋንቋ የእንግሊዝ ቋንቋ ነው። የበለጠ የሕዝቡ ትዳርም እርሻና አታክልት መትከል ነው። የኢንዱስትርያ ዓይነት ሁሉም በዚያ አገር ሰልጥንዋል። ረጃጅምና ወፍራሞች ዛፎች ያሉባቸው፥ ከሁሉ የበለጡ ዱሮች ከአማዙን ሰን ሎሬንሶ ሚሲስፒ የተባሉ ወንዞች አጠገብ ይገኛሉ። እንደ ሚሲሲፒ ያለ ብዞች መርከቦችና ባቡሮች የሚመላለሱበት ወንዝ በዓለም የለም። በዳሩም የሚስተካከለው የሌለበት ዴልታ አለ። በዓለም ካሉ ፍዋፍዋቴ የሚመስለው የሌለ፤ ፷ ሜትር የሚያህል ነያገራ የተባለ ደሞ በሰን ሎሬንስ ወንዝ ነው የሚገኝ። የበለጠ የሚያስደንቅ ደሞ የውሀው ብዛት ነው እንጅ ርዝመቱ ብቻ አይዶለም።

በአሜሪካ ወርቅ ብር፥ አልማዝ መዳብና ብረት የሚመስልም ከነትርፉ ይገኛል። አሜሪካ ከዓለም በሞላው ጋራ ንግድ አለበት።

በዚያ ከመግሥት የተደገፈች ቤተ ክርስቲያን የለም ግን ሁሉ ሰው እንደ ሕሊናው እውነት ሁኖ በተሰማው ልክ፥ እግዚአብሔርን ሊያመልክ በሕግ ተፈቅድዋል። እንደ ባንዳንዱ አገር ልምድ ሁኖ ያለ በሃይማኖት ምክንያት ስደትና ስድብ በዚያ የለም። የአሜሪካ ሕዝብ መንፈሳዊ ሐሳብ ያለበት ሰለ ቤተ ክርስቲያንና በአረማውያን ወንጌል መስበክ ብዙ የሚሰጥ ሕዝብ ነው። አዲስ መንደር የተሰራ እንደሆነም በፊት ቤተ ክርስቲያንና ትምህርት ቤትን የሚሰሩባቸው ስፍሮች ይመረጣሉ። በዚያ አገር ታናናሾች ሊማሩ ስርዓት ነው።

አሜሪካ ከሁለት ታላላቆች ክፍሎች ይከፈላል የሰሜንና የደቡብ አሜሪካ። መንፈሳዊ ብርሃን። የሚደምቅ እውቀት የሚለማ መልካም ስርዓትም የሚገኘት የበለጠ በአሜሪካ ሰሜን ነው።

የአሜሪካ ሕዝብ ሁሉ ፱፻፺፱ ሚልዮን ያህላሉ የሚበዙበቱም ከኤውሮጳ ወገን ናቸው። እነዚያ ኢንድያኒ የተባሉቱ የጥንት አገር ልጆች ናቸው ግን አሁን እያነሱ ይሄዳሉ።

## ካናዳ።

ካናዳ በሰሜን በውቅያኖስ አርቲክን፥ በምዕራብ በስላማዊ ውቅያኖስን በምሥራቅ በውቅያኖስ አትላንቲክ ይገጥማል። ስፋቱ ከኤውሮፓ በሞላው ጥቂት አነስ ይላል። የካናዳ ሕዝብ ፯ ሚልዮንና ፰፻ ሺሕ ናቸው። ያች ቶሮንቶ የተባለች ከተማ ፬፻ ሺሕ ሰዎች አሉባት፥ ዋና ከተማዩቱ ግን ኦታዋ ናት የምትባል። የካናዳ አየር ጤናማ ነው። እነዚያ በሱ ያሉ የሚበዙቱ ከነገደ እንግሊዝ ናቸውና፥ ካባቶቻቸው አገር ጋራ አንድነት አላቸው። ስለዚህም የእንግሊዝ ንጉሥ ለዚያ አገር እንደ ዋናው ነው። የንጉሥ እንደኔ ሁኖ አንድ ጉቤርንር በዚያን አገር ተቀምጠዋል፥ በተቀረው ግን ያገሩን ልጆች በለዚያ በገዛጃቸው የመረጥዋቸው ያገራቸው ልጆች በአርነት ይመራሉ።

## ግሮኤንላንድ።

እርሱ ከካናዳ በስተ ሰሜን ምሥራቅ ነው። ባገሩ የሚሰፍሩም ኤስኪሜዝ የተባሉ ናቸው። ያገሩ ውርጭና ብርድ ብርቱ ነውና፥ የሚበቅለው ነገር የለም። የሚያድንቸው እንደ ዓሣ አንባሪና ፔሼ ካኔ የተባሉ ዓሦች ናቸው የበለጠ ትዳራቸው በነዚሁ ነው። ቈዳቸው ይለብሳሉ ስጋችወን ይበላሉ። በሊበር የብርቱ ብርድ ጊዜያት ቈፍረው ከውርጭ ውስጥ ይሰፍራሉ። ዘመቻ የፈለጉ እንደሆን በውሾች ተጐተው ይሄዳሉ። ግሮኤንላንድ የዳንማርክ ግዛት ነው።

## ሌስ ኤታ ኡኒ ዳሜሪክ።

ሌስ ኤታ ኡኒ ወይስ የአሜሪካ ዩናይትድ ስተትስ የተባበሩት ግዛት ማለት ነው። እሱ ብዙ ነገር እጅግ ሃብታም የሆነ አገር ክፍል ነው። ሕዝቡ እስከ ፺፩ ሚልዮን የሚደርስ ለም ነው። ከተሞቻቸውም በማማራቸው፥ ትልቅነታቸውና የሕዝባቸው ብዛት የሚያስደንቁ ናቸው። መናገሻ ከተማቸው ዋሺንግቶን ናት። ትልልቅ ከተሞችም ኙዮርክ ፬ ሚልዮንና ፯፻ ሺሕ ሰዎች ቺካጎ ፪ ሚልዮንና ፪፻ ሺሕ ሰዎች ፊላዴልፊያ ፩ ሚልዮን ፭፻፶ ሺሕ፥ ሳን ሉዊ ፯፻ ሺሕ ሰዎች አሉዋቸው። ያገሩ አየር የጤና ደስታ ነው። እንደ በሱ ያለ የባቡር ስርዓትም በዓለም የለም።

የሌስ ኤታ ኡኒ አገር በ፵፰ ክፍል ይከፈላል። ሁላቸውም እየሹመኛቸው አላቸው። ከሁሉ በላይ ግን ፕሬሲዴንተ የሚሉት ጠቅላይ ይሾማል። እርሱም በሕዝብ ተመርጦ ለጥቂት ዓመት ይገዛል፥ የተመደበ ጊዜው ከደረሰ በኋላ፥ እንደገና ባይመረጥ፥ ሌላ የተመረጠውን ይሾማል። ከግዛት የሚያግዙትም ሴናቶ የተባሉ ማሕበር አሉ።

## ሜሲክ።

ሜሲክ ከሰሜን አሜሪካ ጋራ የገጠመና በስተ ደቡብም ያለ አገር ነው። ፲፭ ሚልዮንና ፰፻ ሺሕ ሕዝብም ያሉበት ሬፑብሊክ ነው። መናገሻ ከተማዩቱ ፬፻፸ ሺሕ ሰዎች ያሉባት ሜሲክ የተባለች ናት።

# መሀከለኛ አሜሪካ።

መሀከለኛ አሜሪካ ፮ ትንሽ ሬፑብሊኮች አሉት። ስማቸውም ጉኣትማላ፥ ሆንድራስ፥ ሰን ሳልበደር፥ ኒካራጓ፥ ኮስትሪካ፥ ፓናማ ነው። ሕዝቡ ፬ ሚልዮን ተእኩል ናቸው።

# የባሃማ ደሴቶች።

የባሃማ ደሴቶች የተባሉ ከሰሜን አሜሪካና ደቡብ አሜሪካ የሆኑ፥ በስተ ምሥራቅ ከመሀከለኛ አሜሪካ ናቸው ያሉ። የትልልቆቹ ስም ኩባ፥ ሃይቲ፥ ያማይካ፥ ፖርቶሪኮ ነው።

# የደቡብ አሜሪካ።

ታችኛው አሜሪካ ይዞት ያለ ሰው ፶ ሚልዮን ያህላል። ከነዚያ ካያሌ ዓመት በፊት ወደሱ የገቡ ስፓኞችና ፖርቶጌሶች ብዙ ኢንዲያኒ፥ ኔግሪ ሌላ ዓይነት ክልስ የሆኑ ነገድም በዚያ ተቀምጠዋል። ያ አገር በመጀመሪያ በሞላው ከስፓኛና ፖርቶጌስ በታች ይገዛ ነበረ። አሁን ግን ከጉያና በቀር ሁላቸው ከሌላ ግዛት አርነት ወጥተው እየራሳቸው ሬፑብሊካ ሰርተዋል። በሚከተሉት ክፍሎች በየስማቸው እንጠራቸዋለን።

ኮሎምቢያ በሰሜን ዳር ያለ ፬ ሚልዮን ሰዎች ያሉት። መናገሻ ከተማዩቱ ቦጎታ።

ኤኳዶር ከያ በላይ የተጠራ በታች ከውቅያኖስ ፓቺፊክ ዳር ነው። ሕዝቡም ፩ ሚልዮንና ፬፻ ሺሕ ነው። መናገሻ ከተማዩቱ ኩኢቶ።

ፔሩ ፬ ሚልዮንና ፮፻ ሺሕ ሰው አለው መናገሻ ከተማዩቱም ሊማ ናት።

ቦሊቢያ ፪ ሚልዮን ሕዝብ አለው። መናገሻ ከተማዪቱ ላ ፓ ናት።

ሼሌ አንድ ጠባብ ከፔሩ አጠገብ ጀምሮ እስከ ደቡብ አሜሪካ ዳር የሚደርስ ከውቅያኖስ ሰላማዊ ጠረፍ ያለ አገር ነው። ሕዝቡ ፫ ሚልዮንና ፱፻ ሺሕ ነው። መናገሻ ከተማዪቱ ሳንቲኣጎ ትባላለች። ሕዝብዋ ፫፻፴ ሺሕ ነው።

ቤኔሱዌላ በሰሜን ዳር ከባሃማ ደሴቶች በታች ይገኛል። ሕዝቡ ፪ ሚልዮንና ፯፻ ሺሕ ነው። ያች ከባሕር ዳር አጠገብ ያለች፥ መናገሻ ከተማዪቱም ካራካስ ትባላለች።

ጉያና ከቤኔሱዌላ በስተ ምሥራቅ ይገኛል። ከእንግሊዝ ፈረንሳና ሆላንዳ በታችም ይገዛል። ሕዝቡ ፩፻፳፫ ሺሕ ነው።

ብራሲል ስፋቱ እለዚያ በአሜሪካ ደቡብ ያሉትን ሬፑብሊኮች ሁሉ ያህላል። ሕዝቡ ፳፩ ሚልዮንና ተእኵል ይሆናል። መናገሻ ከተማዪቱ ሪዮ ደዣይነሮ ትባላለች ሚልዮን የሚያህሉ ሰዎችም አሉባት።

ፓራጉዋይ የተባለ ፯፻ ሺሕ ሕዝብ ያሉበት አገር፥ በውስጥ ያለ፥ ትንሽ ሬፑብሊክ ነው።

ኡራጉዋይ ከፓራጉዋይ በታች ከውቅያኖስ አትላንቲክ ዳር ያለ ፩ ሚሊዮንና ፩ ሺሕ ሰዎች ያሉበት አገር ነው።

አርጀንቲና ከቦሊብያ ጀምሮ እስከ አሜሪካ ደቡብ ዳር የሚደርስ በታቹ ሾላላ፥ በስተ ላዩ ግን እየሰፋ የሚሄድ አገር ነው። ሕዝቡ ፯ ሚሊዮንና ፰፻ ሺሕ ነው። ያች ማለፍያ ወደብ ያለባትና የንግድ መርከቦች የሚመላለሱባት ፩ ሚልዮንና ፫፻ ሺሕ ሰው ያለባት ቦኔስ ኤረስ ትባለለች።

የደቡብ አሜሪካ በሁሉ ሃብታም የሆነ አገር ነው። ብዙ ወደ ሌላ አገር ሂዶ የሚሸጥ እንጨት ይገኝበታል። የሚታደኑ የዱሮች እንስሳ ሞልተዋል ኮንዶር የሚሉት፥ ከሁላቸው ያፎች የሚበልጥ ትልቅ የሆነ ወፍ በዚያ፥ ይገኛል። ያ ፍሬያም አገር ስንዴ፥ የባሕር ማሽላ፥ ቡን የሹከር አገዳ፥ ካካዎ፥ ሎሚን፥ ናርጌ፥ ሙዝ ጥጥ ሌላ እንዲሁም ያለም ያፈራል። ወርቅና አልማዝም ይገኝበታል። ያገሩ አየር ለሰውነት የሚስማማ ነው።

## ኦቼኣኒኣ።

ኦቼኣኒኣ ያን ትንሹ ክፍል፥ ከዓለም ክፍሎች አምስተኛ ነው። ከሱ ጋራ የሚቈጠሩም ብዞች ትልቆችና ትንሾች ደሴቶች አሉ። የሚቀመጡበት ሰዎች ፴ ሚልዮን ያህላሉ። መሬቱ ብዙ ዓይነት ፍሬ የሚያፈራ አየሩም መልካም ነው። ለነፋሱ ባሕር የሚያፈራ አየሩም መልካም ነው። ለነፋሱ ባሕር የሚያበርደው ስለ ሆነም፥ አየሩ ሃሩር አይበረታበትም።

# አውስትራሊኣ።

የአውስትራሊኣ ስፋት ፲፰ ጊዜ ኢትዮጵያን ነው። በሱ የሚኖሩት ነጮች ፬ ሚልዮን ተእኵል ናቸው። ያገሩ ሕዝብ የተዋረዱ ሕዝብና ናቸው፡ ያ አገር በ፯ ክፍል ይከፈላል። ያች በደቡብ ዳር ያለች የታስማንያ ደሴትም ከሱ ትቈጠራለች። እያንዳንዱ አገር ክፍልም ከሕዝብ የተመረጠ ጎበርነርና ፓርላሜንቶ አለበት። ዋና ከተማዪቱ መልቡርን ትባላለች፥ ፫፻፶ ሺሕ ሰውም አላት።

## አዲስ ጉኢኔአ።

ይህች ትልቅ ደሴት ከእንግሊዝና ከሆላንድ በታች ናት። ያገሩ ልጆች ፓፑዋ ናቸው የሚባሉ እርሳቸው አንድ ተዋጊ ሕዝብ ናቸው የነበሩ። አሁን ግን አያሌ ክርስቲያኖች ሁነዋል። ይህች ደሴት ከላይኛው አውስታሊአ በስተ ዳር ናት።

## አዲስ ሴላንድ።

ሴላንድ ከአውስትራሊአ ምሥራቅ ወገን በጣም የራቀች ደሴት ናት። ሕዝብዋ ፩ ሚልዮን ያህላል። እነዚያ ማኦሪ የተባሉ ጥንታውያን ያገር ልጆች ፶ ሺሕ ያህላሉ። አረማውያን ሳሉ፥ እርስ በርሳቸው ይፋጁ ነበሩ። አሁን የእንግሊዝ ግዛት ሁነዋል። ፩፻ ሺሕ ሰው ያላት ዋና ከተማዪቱ ኦክስላንድ ትባላለች።

## የሰላማዊ ውቅያኖስ ደሴቶች።

የደሴቶቹ ቍጥር ብዙ ነው ስለዚህ በ፫ ጋንታ አድርገን እንጽፋቸዋለን ከአውስትራሊአ ያሉ የሜላኔሲአ ደሴቶች፥ ከሳቸው በላይ የሚክሮኔሲአ ደሴቶች በስተ ምሥራቅ ያሉም የፖሊኔሲአ ደሴቶች ይባላሉ። እኩሌታቸው ከእንግሊዝና ፈረንሳዊ መንግሥት በታች ናቸው። ባንዳንድ ከኒህ ደሴቶችም እሳት የሚያፈልቁ ተራሮች አሉ።

ኦቼኣኒኣ ብዙ ዓይነት እህልና ፍሬ የሚያፈራ፥ የተቸፈገ ዱር ያለበት፥ ብዙ ዓይነት እንስሳም የሚኖሩበት ምድር ነው። ከዚህ አገር ታይተው የማያውቁ ያፎችም በነዚያ ደሴቶች ይገኛሉ። ያ ለማየቱ የሚያስገርም የገነት ወፍ የሚሉት አገሩ ነብ ወይስ አዲስ ጕኢኤአ ነው።

የነዚህ ያመለከትናቸው ደሴቶች አስቀድመው የተዋረዱ በአረሚነት ጨለማ የሚመላለሱ አረማውያን፥ ሰው የሚበሉም ነበሩ። አሁን ግን ላያሌ የደሴቶቹ ሰዎች ወንጌል ተሰብኮላቸዋልና ብዞች ከነሳቸው እውነተኛ አምላክን አውቀው በብርሃኑና በጽድቁ ይመላለሳሉ።

ክብረቱንና እውቀቱንም በሞላው ዓለም ሊዘረጋ ነው።



Olof Werner William Eriksson